ምክንያተ ፡ ጽሒፈቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐርዋ ጎበ ፡ ኤፌሶን ፡ ኮነ ፡ ለአዘክሮ ፡ ብዙኅ ፡ ሀብታት ፡ ዘተውህበ ፡ ለምእመናን ፡ እመንገለ ፡ አሚን ።

ወኤፌሶንኒ ፡ አሐቲ ፡ መክፈልት ፡ ይእቲ ፡ እምዮናናውያን ።

ወርእሰ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘእስያ ፡ በከመ ፡ ኮነት ፡ ቆርንቶስ ፡ ሊቅተ ፡ አካይያ ።

ወነበሩ ፡ በውስቴታ ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ፡ ኅቡረ ።

ወኀዳጣን ፡ እምኔሆሙ ፡ እምኑ ፡ በስብከቱ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ።

ወእምድኅረ ፡ ጉንዱይ ፡ መዋዕል ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወሰበከ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወእምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ኅቡረ ።

ወእመኒ ፡ ሖረ ፡ ጳውሎስ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ ኢጸኑ ፡ በምግባትኒ ፡ እስ ፡ ይበዝኁ ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢኀደገ ፡ ፍቅረ ፡ አሪት ፡ ወኢኀደገ ፡ እምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ዳዕሙ ፡ ወሰኩ ፡ ሠናያተ ፡ ወጸንዑ ፡ በሃይማኖት ።

ወእጸሐፈ ፡ ሎሙ ፡ ዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ በዘይትቃወሞ ፡ ለትምህርተ ፡ ሕይወት ፡ ዳዕሙ ፡ ጸሐፈ ፡ እንዘ ፡ ይዌድሶሙ ፡ ወያሬእዮሙ ፡ በውስቴታ ፡ ከመ ፡ ኅረዮሙ ፡ ሥምረተ ፡ ፈቃዱ ፡ እምቅድመ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሠርዖሙ ፡ በፍቅር ፡ ለትርሲቱ ፡ ወልዱ ።

ወአርአዮሙ ፡ ከመ ፡ እመንቱ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ መዓርግ ፡ ሰማያዊ ፡ ዘይትሌዓል ፡ ፈድፋደ ፡ እመዓርገ ፡ መላእክት ።

ወከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ ርእሶሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ መሌሊተ ፡ ሥጋሁ ።

ወባሕቱ ፡ ኅዳጣን ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢኀደጉ ፡ ሐዊረ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ በኅቡእ ፡ በከመ ፡ ልማድ ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ዝቡሐ ፡ ለአማልክት ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ ከታብ ፡ የጻፈበት ፡ ምክንያት ፡ ከየይማኖት ፡ የተነሣ ፡ ለምእመናን ፡ የተሰጠው ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡ እንደኾነ ፡ ለማሳሰብ ፡ ነው ።

ኤፌሶንም ፡ ከ፪ ፡ የናናውያን ፡ አንዷት ፡ ክፍል ፡ ናት ።

ቆሮንቶስ ፡ ለአካይያ ፡ መዲና ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ ኤፌሶንም ፡ በእስያ ፡ ላሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መዲና ፡ ነበረች ።

በውስጧ ፡ አይሁድም ፡ አረሚም ፡ ባንድነት ፡ ይኖሩባት ፡ ነበረ ።

ከነዚያውም ፡ ጥቂቶቹ ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ስብከት ፡ አምነው ፡ ነበረ ።

ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ የጌታችንን ፡ ስም ፡ ባስተማረ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉም ፡ ባንድነት ፡ አመኑ ።

ጳውሎስም ፡ ከነሱ ፡ ከኼደ ፡ በኋላ ፡ ከነሱ ፡ ብዙዎች ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ በትሩፋት ፡ ላይ ፡ ትሩፋት ፡ ጨመሩ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፍቅረ ፡ ኦሪትም ፡ ኾነ ፡ ወደ ፡ እምልኮ ፡ ጣዖትም ፡ ቢኾን ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ አላዘነበሉም ።

ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ ሲያመሰግናቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍርጥ ፡ ውዱ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ መረጣቸው ፤ በፍቅርም ፡ የልጁ ፡ ጌጦች ፡ አድርጎ ፡ እንዳከናወናቸው ፡ ሲገልጽላቸው ፡ ጻፈላቸው ፡ እንጂ ፡ ትምህርተ ፡ ሕይወት ፡ ወንጌልን ፡ እንደሚቃወሙ ፡ አድርጎ ፡ አልጻፈባቸውም ።

ከመላእክት ፡ መዓርግ ፡ አጅግ ፡ በሚበልጥ ፡ በሰማያዊ ፡ ማዕርግ ፡ እነሱ ፡ እንዳሉ ፡ ገለጠላቸው ።

ክርስቶስ ፡ ለእነሱ ፡ ራሳቸው ፡ እንደኾነ ፡ እነርሱም ፡ ለርሱ ፡ የሥጋው ፡ አባሎች ፡ እንደኾኑ ፡ ገሰጠላቸው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከነሱ ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ለመብላት ፡ በድብቅ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ መሔዳቸውን ፡ አልተዉም ፡ ነበረ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወይመርህ ፡ ዘንተ ፡ በብሂሎቱ ፡ በዝንቱ ፡ መልእክት ፡ አዕትቱ ፡ እምላዕሌክሙ ፡ ግእዘክሙ ዘትካት ፡ እብል ፡ በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ብእሲ ፡ ዘይማስን ፡ በፍትወተ ፡ ስሒት ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፳፫ ።)

ሐድሱ ፡ ልበክሙ ፡ ወልበስዎ ፡ ለሐዲስ ፡ ብእሲ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፳፬ ።)

ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ ኢታምዕዕዎ ፡ ለመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ዘኀዱር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ዘቦቱ ፡ ዐተበክሙ ፡ እመ ፡ ድኅንክሙ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፴ ።)

ወትሩፋኒሆሙኒ ፡ እዘዘ ፡ ከመ ፡ ኢይኅበሩ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ወኢትኅበሩ ፡ ምስለ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ፍሬ ፡ ምግባሮሙ ፡ ዘጽልመት ፡ ዙለንታሆሙ ።

እላ ፡ ኅሥጽዎሙ ፡ እስመ ፡ ዘበጽሚት ፡ ይገብሩ ፡ ኀፍረተ ፡ ለነጊር ።

ወዘሰ ፡ ክሡት ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ይትዐወቅ ፡ እስመ ፡ ዘገሃድ ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ፡

ወፈነወ ፡ ሎሙ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ በእደ፡ ቲቶ ፡ ረድኡ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ሙቁሐ ፡ በሮሜ ፡ እመ ፡ ሙቃሔሁ ፡ ቀዳማዊ ።

ይህን ፡ የቀድሞ ፡ ልማድ ፡ አለመተዋቸውንም ፡ በዚሁ፡ ክታቡ ፡ የቀድሞ ፡ ግብራቸውን ፡ ከናንተ ፡ አርቁ ፡ ይህንም ፡ ኃጢአትን ፡ ጣዖትን፡ በመውደድ ፡ ስለሚለወጥ ፡ ብሉይ ፡ ሰውነት ፡ እናገራለሁ ።

ልቡናችሁን ፡ በዕውቀት ፡ አድሳችሁ ፡ ሐዲስ፡ ብእሲ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ምሳሌት ፡ በማለቱ፡ ያስረዳል ።

ስለዚህም ፡ ባመናችሁ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ እናንተን ፡ ያከበሩበትን ፡ አድርባችሁ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አታሳዝኑት ፡ አለ ።

የቀሩትም ፡ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ እንዳይተባበሩ ፡ ሥራቸው ፡ እፍን ፡ ጭፍን ፡ ያለ ፡ የበጎ ፡ ምግባር፡ ፍሬ ፡ ከሌላቸው ፡ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አትኹኑ፡

በቀበታ ፡ በቆይታ ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሊናገሩት ፡ የሚያሳፍር ፡ ነውና ፡ ገሥጿቸው ፡ እንጂ ፡ አትተባበሯቸው ።

በግልጥ ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ነውና ፡ በግልጽ ፡ በመሠራቱ ፡ እውነትነቱ ፡ ይታወቃል፡ ብሎ ፡ መከራቸው ።

ይህን ፡ ክታብ ፤ በመጀመሪያ ፡ እስራቱ ፡ በሮም ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ በደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ በቲቶ እጅ ፡ ላከላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ን ኤፌሶን ፡ ምድረ ፡ ጽርእ ፡ ናት ፡ ቀጥሯም ፡ ከሰባቱ ፡ የናናውያን ፡ ነው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ገብቶ ፡
ጌታ ፡ ከዕንስ ፡ ጀምሮ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራውን ፡ ትሩፋት ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡
ቢነግራቸው ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደገቢረ ፡
ጽድቅ ፡ ተመለሱ ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ ፡ ትምህርት ፡ ካልደረሰባት ፡ ለማዳረስ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ሲያስተ
ምር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደረሰ ። በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡበት ፡ በሉስዮስ ፡
ዳኝነት ፡ ያዙት ። ከዚያም ፡ ከፊልክስ ፡ ዘንድ ፡ ይወርዳል ፡ በፊልክስ ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ይታስ
ራል ። ፊልክስ ፡ ተሽሮ ፡ ፊስጦስ ፡ ቢሾም ፡ ሮም ፡ በመጋቢያ ፡ ይወርዳል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳ
ውያን ፡ ገብተው ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ ኦሪት ፡ ጥምቀት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡
ብለዋቸዋል ። እነዚያም ፡ መንፈሳውያን ፡ ከኾኑ ፡ በኋላ ፡ ሥጋውያን ፤ ሰማያውያን ፡ ከኾኑ ፡ በኋላ ፡ ምድ
ራውያን ፡ መኾን ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ብለው ፡ እንደገላትያ ፡ ሰዎች ፡ ተጨልጠው ፡ ተገርኝተው ፡
አልሔዱም ፡ ባሉበት ፡ ጸንተዋል ። ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ሲያመሰግን ፡ ጽፎ ፡ ይሰድላቸዋል ። ይትባረክ ፡
እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘባረከነ ፡ በኵሉ ፡ በረከተ ፡ መንፈስ ፡ በሰማ
ያት ፡ በክርስቶስ ፡ በኢየሱስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፫ ።)
ወበእንተዝ ፡ እነሂ ፡ ሰሚዕየ ፡ ሃይማኖተክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወዘከመ ፡ ታፈቅ
ርዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ኢያንተጉ ፡ እዕኵቶቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአክሙ ፡ ወተዘክሮ
ተክሙ ፡ በጸሎትየ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አበ ፡ ስብሐት ።
(ም ፡ ፩ ፡ ፲፭ ፡) እምይእዜሰ ፡ ኢኮንክሙ ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ፡ አላ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገሪቶሙ ፡ ለቅ
ዱሳን ፡ ወሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፱) እብል ፡ በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ብእሲ ፡ ዘይማስን
በፍትወተ ፡ ስሒት ፡ ሐድሱ ፡ መንፈሰ ፡ ልብክሙ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፳፪) ዘይሰርቅኒ ፡ ኢይሰርቅ ፡ እንከ ፡ ዳዕሙ
ለይትገበር ፡ ወይጻሙ ፡ እንከ ፡ በእደዊሁ ፡ ለሠናይ ፡ በዘይረድእ ፡ ለነዳይ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፳፱) ከዚህ ፡ በኋላ
ሠሪዐ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ ወዘትፈቅዱስ ፡ ታእምሩ ፡ ዜናየ ፡ ያጤይቀክሙ ፡ ጢኪቆስ ፡ እኁነ ፡ ዘናፈቅር ፡
ዘከመ ፡ እገብር ፡ ኵሉ ፡ ጸጋሁ ፡ በኢጥፍዐት ፤ ይላል ፡ የጻፈበት ፡ ሀገር ፡ ሮም ፡ ከታብ ፡ ወሳጅ ፡ ጢኪቆስ

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ።
በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሾመኝ ፡ አንድም ፡ ሰውን ፡ አጸና
ዘንድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ከማስተምር ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ መልእክት ።
ለቅዱሳን ፡ እለ ፡ በኤፌሶን ፡ ወምእመናን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፯ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፪ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምነው ፡ በኤፌሶን ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ትድረስ ።
፪ ፡ ሰላም ፡ ለከሙ ፡ (ቸር ፡ አላችሁን ፡
ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የእግዚአብሔር ፡ የአባታችን ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የጌታችን ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ይደረግላችሁ ።
፫ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የጌታችን ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።
ዘባረከነ ፡ በኵሉ ፡ በረከተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሰማያት ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፯ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካሣ ፡ በልዕልና ፡ ለመኖር ፡ መንፈሳዊ ፡ ብዛት ፡ ያበዛል ፡ ብዝኀ ፡ ወተባዝኁ ፡
ቢል ፡ ያ ፡ ሥጋዊ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ ነውና ። አንድም ፡ መንፈሳዊ ፡ ክብር ፡ ያክበረን ፤
ወአውፅኦሙ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ቢል ፡ ያ ፡ ሥጋዊ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ ነውና ።
፬ ፡ በከመ ፡ ኀረየነ ፡ ሎቱ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ (ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፱ ። ም ፡
፭ ፡ ፳፯ ።)
ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፤ (ሎቱ) ፡ ለሱ ፡ አካል ፡ ብልት ፡ ማኅበር ፡ ቤት ፡ ሰብእ ፡ ለመኾን ፡ እንደመረጠን ።
እንድም ፡ (ሎቱ) ልርስቱ ፡ ለጕልቱ ፡ ለመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ እንደመረጠን ፡ መጠን ።
፭ ፡ ይረስየነ ፡ ቅዱሳነ ፡ ወንጹሓነ ፡ በቅድሜሁ ፡ በተፋቅሮ ።
በፍቅር ፡ ኾነን ፡ በፊቱ ፡ ለመቆም ፤ እንድም ፡ በቅድሜሁ ፤ ባለሟሎች ፡
ለመኾን ፡ ንጹሓን ፡ ክቡራን ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ።
፮ ፡ ወሠርዐነ ፡ ትርሲተ ፡ ወልዱ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በከመ ፡ ሥምረተ ፡ ፈቃዱ ። (ገላ ፡
ሐዋ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።)
(ዘባረከነ ፤ ወዘሠርዐነ ፡ በፍቅር) ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለካሰልን ፡ የልጅነትን ፡ ጌዋ ፡ ያዘጋጀልን ፤

www.ethiopianorthodox.org

(ትርሲተ ፡ ወልዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ) እንደቁርጽ ፡ ውዱ ፡ የልጁ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌጥ ፡ አድ ርጎ ፡ ያከናወነን ።

፮ ፡ ስከብር ፡ ወስብሐት ፡ ለጸጋሁ ፡ ዘጸገወነ ፡ በወልዱ ፡ ፍቁሩ ። (ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።)
(ሠርዐነ ፡ ለክብር ፡ ወለስብሐት) ፡ በልጁ ፡ በወዳጁ ፡ ባደረገው ፡ በቸርነቱ ፡ ለክብር ፡ ለጌትነት ፡ ያከናወነን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፯ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ረከብነ ፡ መድኃኒተ ። (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።)
እሱ ፡ ስለካሰልን ፡ ድኅነትን ፡ ያገኘንበት ።

ወተኀድገ ፡ ለነ ፡ ኃጢአትነ ፡ በደሙ ።
በደሙ ፡ ኃጢአታችን ፡ የተሰረየበት ።

፰ ፡ በከመ ፡ ብዕለ ፡ ጸጋሁ ፡ ዘአፈድፈደ ፡ ላዕሌነ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፯ ፡ ፮ና ፤ ፫ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ።)
ለኛ ፡ አብዝቶ ፡ እንዳደረገው ፡ እንደቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ መጠን ።

በኵሉ ፡ ጥበብ ፡ ወምክር ።
(ጥበብ ፡) በፍጹም ፡ እውነት ፡ (ምክር ፡) ፈሊጥ ። እንድም ፡ (ጥበብ ፡) አንድነት ፡ ሦስትነት ፡ (ምክር) ሥጋዌ ።

፱ ፡ ወአርአየነ ፡ ምክረ ፡ ፈቃዱ ፡ በከመ ፡ ሥምረቱ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፱ ፡ ሮሜ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ።)
ዘባረከነ ፡ ወዘሠርዐነ ፡ ወዘአርአየነ ፡ ይላል ፡ እስከዚህ ፡ ይወርዳል ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የውድ ፡ ነው ። ፈቃዱ ፡ እንደመኾኑ ፡ ወዶ ፡ መክሮ ፡ ያደረገ ፡ ያደረገውን ፡ የሥጋዌውን ፡ ምሥጢር ፡ የገለጠልን ፡

ወሠርዐነ ፡ በእንቲአሁ ።
እኛን ፡ ያከናወነበት ።

፲ ፡ ወዐቀመ ፡ በዘይበጽሕ ፡ ዕድሜሁ ፡ ከመ ፡ ይትሐደስ ፡ ኵሉ ፡ ዘበሰማይ ፡ ወዘበምድር ።
በሰማይ ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ይታደስ ፡ ዘንድ ፡ የሚታደስበት ፡ ጊዜው ፡ እስቲደርስ ፡ የወሰነው ጊዜው ፡ ቢደርስ ፡ የፈጸመው ፡ መመለክ ፡ ብልዩት ፡ አለመመለክ ፡ ተሐድሶ ፡ ነውና ። እንድም ፡ በዐጸደ ሥጋ ፡ በዐጸደ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ይታደስ ፡ ዘንድ ፡ የሚታደስበት ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ የወሰ ነው ፡ ጊዜው ፡ ቢደርስ ፡ የፈጸመው ።

፲፩ ፡ ወከፈለነ ፡ በዘሠርዐነ ፡ እግዚአብሔር ። (ገላት ፡ ፬ ፡ ፬ ።)
እግዚአብሔር ፡ ባከናወነን ፡ ገንዘብ ፡ ያከናወነበትን ፡ ግብር ፡ ያደለን ።

ወረድአነ ፡ በከመ ፡ ምክረ ፡ ፈቃዱ ።
ወዶ ፡ መክሮ ፡ ባደረገው ፡ ሥጋዌ ፡ ያዳነን ፡ መጽአ ፡ ወረድአሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔገሉሙ ፡ ሰይጣን ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፴፰) ። እስመ ፡ በዘአመከርዎ ፡ ወአሕመምዎ ፡ ክህለ ፡ ረድኤቶሙ ፡ ለሕሙማን ፡ እን ዲል ፡ (ዕብ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ።)

፲፪ ፡ ከመ ፡ የሀበነ ፡ ምክረ ፡ ወስብሐተ ፡ ለእለ ፡ ተወከልነ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ (ገላት ፡ ፳፫ ፡ ፳፭ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ላመነ ፡ ለኛ ፡ ክብርን ፡ ጌትነትን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ።

፲፫ ፡ ወአንትሙኒ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ ትምህርተ ፡ ሕይወትክሙ ፡ ወአመንክሙ ።
ባረከነ ፡ ሠርዐነ ፡ አርአየነ ፡ ረድአነ ፡ እያለ ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፡ የራሱን ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ የኛን ፡ ምን ፡ ተናገረ ፡ እንዳይሉት ፡ እናንተም ፡ ድኅነት ፡ የሚገኝበት ፡ እውነተኛ ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ ሰምታችሁ ፡ አምናችኋል ።

ወዐቀቡክሙ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘአሰፈወ ። (ም ፡ ፪ ፡ ፴ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ።)
ያመናችሁ ፡ እናንተንም ፡ እሠውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ብሎ ፡ ባናገረው ፡ በመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍትሖ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ከኢአማንያን ፡ ለይቶ ፡ ቀሟችኋል ፡ ራሳቸውን ፡ አስመስለዋችኋል ።

፲፬ ፡ ዘውእቱ ፡ ዐረቦነ ፡ ርስትነ ፡ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ።)
የርስታችን ፡ ፈለግ ፡ የሚኾን ፡ ብሎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይቀጥላል ።

ወመድኃኒተ ፡ ሕይወትነ ፡ በክብረ ፡ ስብሐቲሁ ።
የነፍሳችንም ፡ ድኅነት ፡ የሚኾን ። እንድም ፡ (ዐረቦነ ፡ ርስትነ ፡) የርስታችን ፡ ፈለግ ፡ የሚኾን ።

www.ethiopianorthodox.org

ወመድኃኒተ ፡ ሕይወትነ ፡ በክብረ ፡ ስብሐቲሁ ።

(ወዐረበነ ፡ መድኃኒትነ ፡ በክብረ ፡ ስብሐቲሁ ፡) ይላል ፡ በባሕርዩ ፡ ክብሩ ፡ የትንሣኤያችን ፡ ፈለግ የሚኾን ። ይህንም ፡ ቄርሎስ ፡ በምክሐ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ።

## ክ ፍ ል ፪ ።

፲፭ ፡ ወበእንተዝ ፡ እነሂ ፡ ሰሚዕየ ፡ ሃይማኖተክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

እኔም ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማመናችሁን ።

ወዘከመ ፡ ታፈቅርዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ። (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፬ ።)

ምእመናንንም ፡ መውደዳችሁን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፤ ሰምቼ ። አንድም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳ መናችሁ ፡ ምእመናንንም ፡ እንደወደዳችሁ ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፤ ሰምቼ ።

፲፮ ፡ ኢያንተጉ ፡ እእኵቶ ፡ በእንቲአክሙ ።

ስለዚህ ፡ ስለናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማመስገንን ፡ አላቋረጥኩም ።

ወተዘክሮተክሙ ፡ በጸሎትየ ። (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲ ።)

በምጸልየውም ፡ ጸሎት ፡ እናንተን ፡ ማሰብ ፡ አልተውም ።

፲፯ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ።

አበ ፡ ስብሐት ፡ (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፬ ።)

አምላኩ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እንዳይሉበት ፡ አበ ፡ ስብሐት ፡ ብሎ ፡ ለወልድ ፡ ቀጠለ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የሚኾን ።

የሀብክሙ ፡ መንፈስ ፡ ጥበብ ።

አንድነትን ፡ ሦስትነትን ፡ የምታውቁበትን ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ ኢያንተጉ ።

ወይክሥት ፡ ለክሙ ፡ ታእምሩ ።

ዕውቀትን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ።

፲፰ ፡ ወያብርህ ፡ አዕይንተ ፡ ልብክሙ ፡ (፪ ፡ ቆር ፡ ፬ ፡ ፬ ።)

ዓይነ ፡ ልቡናችሁንም ፡ ያበራላችሁ ፡ ዘንድ ።

ወታእምሩ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ተስፋሁ ፡ ለጽዋዔክሙ ።

በሃይማኖት ፡ ነው ፡ ትልውኒ ፡ ተብላችሁ ፡ የተጠራችሁት ፡ አጠራር ፡ ተስፋው ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ (እለ ፡) ፡ ደግ ፡ እንደኾነ ፡ ልታወቁ ፡ እውቀትን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ በወልድ ፡ ውሉድ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብላችሁ ፡ የተጠራችሁት ። አጠራር ፡ ተስፋው ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ (እለ) ፡ ደግ ፡ እንደኾነ ፡ ልታውቁ ። አንድም ፡ ኋላ ፡ ነው ፡ ኀቤየ ፡ ቡሩካን ፡ ለአቡየ ፡ ተብላችሁ ፡ የምትጠሩት ፡ አጠራር ፡ ተስፋው ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ (እለ) ፡ ደግ ፡ እንደኾነ ፡ ልታውቁ ፡ ዕውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ።

ወምንት ፡ ውእቱ ፡ ብዕለ ፡ ስብሐተ ፡ ርስቶሙ ፡ ለቅዱሳን ።

ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ የሚወርሷት ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ክብር ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ (እለ ፡) ደግ ፡ እንደኾነ ፡ ልታውቁ ፡ እውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ።

፲፱ ፡ ወምንት ፡ ፍድፋዴ ፡ ጽንዐ ፡ ኃይሉ ፡ ዘላዕሌነ ፡ ለእለ ፡ ነአምን ።

ባመነ ፡ በኛ ፡ አድሮ ፡ ያደረገው ፡ የተአምራቱ ፡ ምላት ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ (እለ) ፡ ደግ ፡ እንደ ኾነ ፡ ልታውቁ ፡ እውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ።

በከመ ፡ ዕበየ ፡ ኃይሉ ፡ ዘገብረ ፡ በክርስቶስ ።

በክርስቶስ ፡ ሀልው ፡ ኾኖ ፡ እንዳደረገው ፡ እንደታምራቱ ፡ ብዛት ።

አንድም ፡ ወምንት ፡ ፍድፋዴ ፡ ጽንዐ ፡ ኃይሉ ፡ ዘላዕሌነ ፡ ለእለ ፡ ነአምን ።

ባመነ ፡ በኛ ፡ አድሮ ፡ በከሀሊነቱ ፡ ያደረገው ፡ የተአምራቱ ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ልታውቁ ፡ እውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ።

በከመ ፡ ዕበየ ፡ ኃይሉ ፡ ዘገብረ ፡ ለክርስቶስ ።

በክርስቶስ ፡ ሀልው ፡ ኾኖ ፡ በከሀሊነቱ ፡ እንዳደረገው ፡ እንደ ፡ ተአምራቱ ፡ ብዛት ።

www.ethiopianorthodox.org

፳ ፡ ዘአንሥኦ ፡ እሙታን ።
ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ባስነሣው ።
ወአንበሮ ፡ በየማኑ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ (መዝ ፡ ፻ ፡ ፲ ፡ ፩ ።)
በልዕልና ፡ በዕሪናው ፡ ባኖረው ፡ በክርስቶስ ፡ ሀልው ፡ ኾኖ ፡ (ለን ፡ ለእለ ፡ ንአምን ፡) ላመነ ፡ ለኛ ፡ ያደረገው ፡ የተአምራቱ ፡ ምላት ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ልታውቁ ።
(በከመ ፡ ዕበየ ፡ ኃይሉ ፡ ዘገብረ ፡ ለክርስቶስ ።)
ለክርስቶስ ፡ እንዳደረገው ፡ እንደተአምራቱ ፡ ብዛት ። (ለነ ፡ ለእለ ፡ ነአምን ፤ ዘገብረ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ ኹለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ። ለኹለቱም ፡ ያመጣል ።
ዘአንሥኦ ፡ እሙታን ።
ዘገብረ ፡ በክርስቶስ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡ ይኸውም ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ያስነሣው ፡ ማስነሣት ፡ ነው ።
ወአንበሮ ፡ በየማኑ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ።
በልዕልና ፡ በዕሪናው ፡ ያኖረው ፡ ማኖር ፡ ነው ።
፳፩ ፡ መልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ መላእክት ።
ከመላእክት ፡ በላይ ።
ወመኳንንት ፡ ወኃይላት ፡ ወእጋእዝት ።
መኳንንት ፡ ኃይላት ፡ እጋእዝት ፡ ስመ ፡ ነገድ ፡ ነው ።
ወኵሉ ፡ ስም ፡ ዘይሰመይ ።
እለ ፡ ኢይብልዎሙ ፡ እገሌ ፡ ወእገሌ ።
ወአኮ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ባሕቲቱ ።
ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ያደረገው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
ወባሕቱ ፡ በዘይመጽእኒ ፡ ዓለም ። (ቈላ ፡ ፪ ፡ ፲ ።)
በሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፳፪ ፡ ወኵሎ ፡ አግረረ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ።
ኹሉን ፡ በእግሩ ፡ እርግጥ ፡ በእጁ ፡ ጭብጥ ፡ አድርጎ ፡ አስገዛለት ፡
ወኪያሁ ፡ ዘውእቱ ፡ መልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ ረሰዮ ፡ ርእሰ ፡ ስቤተ ፡ ክርስቲያን ። (ም ፡ ፬ ፡ ፲፭ ፡ መዝ ፡ ፰ ፡ ፮ ፡ ፰ ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ።)
ከኹሉ ፡ በላይ ፡ የሚኾን ፡ እሱን ፡ ለምእመናን ፡ ገዥ ፡ ጌታ ፡ አደረገው ።
፳፫ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሥጋሁ ። (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ።)
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያላትን ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሥጋሁ ፤ ይችውም ፡ አካሉ ፡ ናት ።
ወውእቱ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ለኵሉ ።
ለኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚኾን ፡ ብሎ ፡ ርእስ ፡ ላለው ፡ ይቀጥላል ።
ወይፌጽም ፡ ኵሎ ፡ በኵሉ ። (ም ፡ ፬ ፡ ፲ ።)
ኹሉን ፡ በኹሉ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰውን ፡ በሀብት ፤ ሀብቱን ፡ በሰው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፪ ።

## ክ ፍ ል ፡ ፫ ።

፩ ፡ ወአንትሙኒ ፡ እንዘ ፡ ምውታን ፡ አንትሙ ፡ በኃጢአትክሙ ፡ (ቈላ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡)
እናንተም ፡ ከሱ ፡ አንድነት ፡ ተለይታችሁ ፡ የነበረ ።
፪ ፡ በዘቦቱ ፡ ሖርከሙ ፡ ትካት ።
ቀድሞ ፡ በነበራችሁበት ፡ በኃጢአታችሁ ፡ ነው ፤ በንብረተ ፡ ሥርዓተዝ ፡ ዓለም ፡ ማንሻ ።
በንብረተ ፡ ሥርዓት ፡ ዝ ፡ ዓለም ።
እንድም ፡ ቀድሞ ፡ በነበራችሁበት ፡ በኃጢአታችሁ ፡ ከሱ ፡ አንድነት ፡ ተለይታችሁ ፡ የነበረ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥርዓት ፡ እንኖር ፡ ነው ፡ ከመ ፡ ሥምረተ ፡ መልአክ ፡ ማንሻ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ሥምረተ ፡ መልአከ ።
አንድም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥርዓት ፡ እንኖር ፡ ቀድሞ ፡ በኀበራችሁበት ፡ በኃጢአታችሁ ፡ ከሱ ፡ አን
ድነት ፡ ተለይታችሁ ፡ የነበረ ፡ እንደዚህ ፡ ዓለም ፡ አበጋዝ ፡ እንደ ፡ ዲያብሎስ ፡ ፍርድ ፡ ውድ ፡ ነው ።
መኰንን ፡ ርእየተ ፡ ነፋስ ፡ (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ፡ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ።)
ዓለመ ፡ ነፋሳትን ፡ የሚገዛ ። ሐተታ ፡ ሳይሻር ፡ ሹመቱ ፡ መጋቢ ፡ ነፋሳት ፡ ነበረና ፡ አንድም ፡ ባሕ
ርዩ ፡ ነፋሳት ፡ ያለው ፤ ተፈጥሮው ፡ ከእሳት ፡ ከነፋስ ፡ ነውና ፡ ወሶበ ፡ ኢያዕኰትኮ ፡ ለዘፈጠረከ ፡ እም
ነበልባለ ፡ እሳት ፡ ወእምነፋስ ፡ ፈጠረ ፡ ህየንቴከ ፡ ሰብአ ፡ ዘማሬ ፡ እግዚ ፡ ወእመሬት ፡ እንዲል ፡
(መቃብያን ፡) አንድም ፡ መልክአ ፡ ነፋሳት ፡ ያለው ፡ እስመ ፡ ነፋስ ፡ ጸሊም ፡ በአርአያሁ ፡ እንዲል ፡
በእርአያሁ ፡ እንዲል ፡ (ጌና ።)
ዘይትኤዘዝ ፡ ይእዜ ፡ ለደቂቀ ፡ ከሃድያን ።
ለደቂቅ ፡ ከሃድያን ፡ ለደቂቀ ፡ ከሃድያን ፡ ይላል ።
ዛሬ ፡ በከሃድያን ፡ ልጆች ፡ የሚበራታባቸው ። ወዙሉ ፡ ወርቀ ፡ ባሕር ፡ ከመ ፡ ጽቡር ፡ በኀቤሁ ፡
እንዲል ፡ ኢዮ ፡ ፵፩ ፡ ፳፩ ።
ቀድሞ ፡ በኵሉ ፡ ነበረ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ በከሃድያን ፡ ልጆች ፡ ነውና ፡ ዘይትኤዘዝ ፡ ይእዜ ፡ ለደቂቀ ፡
ከሃድያን ፡ አለ ።
፫ ፡ ወንሕነሂ ፡ ነበርነ ፡ ትካት ፡ በፍትወተ ፡ ሥጋነ ።
እኛም ፡ ቀድሞ ፡ በፈቃደ ፡ ሥጋችን ፡ እንኖር ፡ ነበር ።
ወገበርነ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋነ ።
ፈቃደ ፡ ሥጋችንን ፡ እንሠራ ፡ ነበር ።
ወዘሐለይነ ።
የወደድነውን ፡ ኹሉ ፡ እንሠራ ፡ ነበር ።
ወኮነ ፡ ውሉደ ፡ መንሡት ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ኃጥአን ።
እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ጥፋት ፡ የሚገባን ፡ ልጆች ፡ ኾነን ፡ ነበር ።
፬ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ በብዕለ ፡ ሰብሐቲሁ ፡ ወበብዝኀ ፡ ፍቅሩ ፡ ዘአፍቀረነ ።
እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እኛን ፡ ባፈቀረበት ፡ በፍቅሩ ፡ ጽናት ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ።
፭ ፡ እንዘ ፡ ምውታን ፡ ንሕነ ፡ በኃጢአትነ ፡ አሕየወነ ፡ በክርስቶስ ።
በኃጢአታችን ፡ ምውታን ፡ ስንኾን ፡ በክርስቶስ ፤ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ አስነሣን ።
ወድኅነ ፡ በጸጋሁ ፡ (ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፳፬ ፡ ፴፪ ።)
ሰነ ፡ ለእለ ፡ ነአምን ፡ ላለው ፡ እርእሰት ፡ አመጣ ። በቸርነቱ ፡ ከኃጢአት ፡ ዳን ።
፮ ፡ ወአንሥአነ ፡ ወአንበረነ ፡ ምስሌሁ ፡ በሰማያት ፡ በኢየሱ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲ ፡ ፊል ፡ ፫ ፡ ፳ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ አስነሥቶ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ለመኖር ፡ በሰማያዊ ፡
ግብር ፡ አኖረን ።
፯ ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ በዓለም ፡ ዘይመጽእ ፡ ብዝኀ ፡ ጸጋሁ ፡ ወምሕረቱ ፡ ዘአፈድፈደ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
( ም ፩ ፯ )
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አብዝቶ ፡ ያደረገውን ፡ የቸርነቱን ፡ ብዛት ፡ እስኪገልጥ ፡ (እስ) በሚመጣው
ዓለም ፡ ትንሣኤ ፡ ሥጋችንን ፡ እስቲገልጥ ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ አስነሥቶ ፡ በሰማያዊ ፡ ግብር ፡ አንበረነ።
አንድም ፡ መልስ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ በብዕለ ፡ ሰብሐቲሁ ፡ ወበብዝኀ ፡ ፍቅሩ ፡ ዘአፍቀረነ ።
እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እኛን ፡ ባፈቀረበት ፡ በፍቅሩ ፡ ጽናት ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ።
እንዘ ፡ ምውታን ፡ ንሕነ ፡ በኃጢአትነ ፡ አሕየወነ ፡ በክርስቶስ ።
በኃጢአታችን ፡ ምውታን ፡ ስንኾን ፡ በክርስቶስ ፤ ትንሣኤ ፡ ሥጋ ፡ አስነሣን ። ፡ ወድኅነ ፡ በጸጋሁ ።
በቸርነቱ ፡ ከሙስና ፡ መቃብር ፡ ዳን ።
ወአንሥአነ ፡ ወአንበረነ ፡ ምስሌሁ ፡ በሰማያት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ በዓለም ፡ ዘይመጽእ ፡
ብዝኃ ፤ ጸጋሁ ፡ ወምኅረቱ ፡ ዘአፈድፈደ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አብዝቶ ፡ ያደረገውን ፡ የቸርነቱን ፡ ብዛት ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ ይገልጥ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ ፡ (ማለት ፡) ትንግኤ ፡ ሥጋችንን ፡ ይገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ትንሣኤ ፡ ሥጋ ፡ አስነሥቶ ፡ በዕሪናው ፡ አኖ
ረን ፡ (ሐተታ) ፡ የሱን ፡ ትንሣኤ ፡ ልኖ ፡ ሰጥቶ ፤ ባሕርዩ ፡ ባሕርያችን ፡ ነውና ።
ተንሥአ ፡ ከመ ፡ ይምሐረነ ፡ ተንሥአ ፡ ሥጋቲነ ፡ ዐርገ ፡ ከመ ፡ ያለቡ ፡ ዕርገተ ፡ ጻድቃን ፡ ንጹሓን ፡
አንጺል ፡ (መቅ ፡ ወን ።)

፰ ፡ እስመ ፡ በጸጋሁ ፡ ድኅነ ፡ ወበአሚን ።
በቸርነቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ድነናልና ።

ወዳዕሙ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ።
ያዳነንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወኢኮነ ፡ ዚአክሙ ፡ (ገላትያ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።)
በናንት ፤ በሙያችሁ ፡ በጉልበታችሁ ፡ አይደለም ።

፱ ፡ ወአኮ ፡ በምግባሪነ ።
በኛም ፡ በሙያችን ፡ በጉልበታችን ፡ አይደለም ።

ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይትሜካሕ ፡ (፩ ፡ ቆር ፡ ፩ ፡ ፳፱ ።)
በሙያዬ ፡ በጉልበቴ ፡ እያለ ፡ የሚመካ ፡ እንዳይኖር ።

፲ ፡ እስመ ፡ ተግባሩ ፡ ንሕነ ፡ ዘፈጠረነ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለምግባረ ፡ ሠናይ ።
በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሐዲስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ለበጎ ፡ ምግባር ፡ የፈጠረን ፡ ፍጥረቶቹ ፡ ነንና፡
በሙያዬ ፡ በጉልበቴ ፡ እያለ ፡ የሚመካ ፡ እንዳይኖር ።

ዘአቅደመ ፡ ሠሪዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስዘቦቱ ፡ ንሐውር ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።)
በሱ ፡ በማመን ፡ ጸንተን ፡ በምንኖር ፡ ገንዘብ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ለሠራው ፡ ለበጎው ፡ ምግባር ።

፲፩ ፡ ወተዘከሩ ፡ አንትሙ ፡ አሕዛብ ፡ ትካት ፡ በሕግ ፡ ዘሥጋ ፡ ሀሉክሙ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፰ ።)
እናንተም ፡ አሕዛብ ፡ ቀድሞ ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ ፡ ግብር ፡ ትኖሩ ፡ እንደነበረ ፡ አወቁ ።
ወይብሉክሙ ፡ ሰብአ ፡ ቈልፈት ፡ ክመዝ ፡ ይብሉክሙ ፡ ሰብአ ፡ ግዝረት ።
ይበሉክሙና ፡ ይብሉክሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሰብአ ፡ ግዝረት ፤ ሰብአ ፡ ቈልፈት ፡ ይሏችሁ ፡ እንደነበረ ።
አንድም ፡ በየራስ ፡ ለማውጣት ፤ ሰብአ ፡ ግዝረት ፡ ሰብአ ፡ ቈልፈት ፡ ይሏችኋል ፡ ይሏችሁ ፡ እንደነበረ፡
አስቡ ።

ወግዝረትሰ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትገበር ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ፡
ግዝረትስ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

፲፪ ፡ ወኢተአምርዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ውእተ ፡ አሚረ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስን ፡ አታውቁትም ፡ ነበር ፡ አታውቁት ፡ እንደነበረ ፡ አስቡ ።

ወነኪራን ፡ አንትሙ ፡ እምሕገ ፡ እስራኤል ፡ (ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፬ ።)
ከእስራኤል ፡ ሕግ ፡ ከአሪት ፡ ልዩ ፡ ነበራችሁ ፡ ልዩ ፡ እንደነበራችሁ ፡ አስቡ ።

ወነግዳን ፡ እምሥርዓተ ፡ ተስፋ ።
ከተነገረው ፡ ተስፋ ፡ መጻተኞች ፡ ስደተኞች ፡ ነበራችሁ ።

ወአልብክሙ ፡ ተስፋ ።
ተስፋ ፡ አልነበራችሁም ።

ወኢተአምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በውስተ ፡ ዓለም ።
በዓለማዊ ፡ ግብር ፡ አየኖረችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አታውቁትም ፡ ነበር ፡ አታውቁት ፡ እንደነበረ ፡
አስቡ ።

፲፫ ፡ ወይእዜሰ ፡ ባሕቱ ፡ አንትሙ ፡ እለ ፡ ትካት ፡ ርኁቃን ፡ ቀረብክሙ ፡ በደሙ ፡ ለክርስቶስ ።
ዛሬ ፡ ግን ፡ ቀድሞ ፡ ከተስፋው ፡ ርቃችሁ ፡ የነበራችሁ ፡ እናንት ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ ወደተስፋው ፡
ቀርባችኋል ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሰላምነ ፡ ዘረሰዮሙ ፡ አሐደ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ (ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ፡ ገላ ፡ ፫ ፡ ፳፰ ።)
ሕዝብና ፡ አሕዛብን ፡ አንድ ፡ ያደረገ ፡ አስታራቂያችን ፡ እሱ ፡ ነውና

www.ethiopianorthodox.org

ወነሠተ ፡ አረፍተ ፡ ማእከል ፡ በሥጋሁ ።

በሥጋው ፡ ክሶ ፡ ኃጢአትን ፡ አጠፋ ፡ (ሐተታ) ፡ ፀረፍት ፡ ማእከል ፡ አላት ፡ ኃጢአትን ፡ ግድግዳ ፡ በመካከል ፡ ኾና ፡ የወዲያውንና ፡ የወዲሁን ፡ እንዳያስተያይ ፡ ኃጢአትም ፡ በመካከል ፡ ኾና ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ ጋራ ፡ መተያየትን ፡ ክልክላን ፡ ነበርና ። እንድም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ ከመኾን ፡ ክልክላ ፡ ነበርና ።

፲፭ ፡ ወሠዓረ ፡ ጽልዐ ፡ (ቈላ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)

ጽልዕን ፡ አጠፋ ፡ (አለ ፡) መለያየትን

ወአብጠለ ፡ ሕገ ፡ ትእዛዝ ፡ በሥርዓቱ ።

ዘአምነ ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፡ ባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ኢትጥዐምንና ፡ ኢትልከፍን ፡ አጠፋ ።

ከመ ፡ ይረስዮሙ ፡ አሐደ ፡ ሐዲሰ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።)

ኹለቱንም ፡ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ።

ወገብረ ፡ ሰላመ ፡

እስታረቃቸው ።

፲፮ ፡ ወእብጽሖሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ በአሐዱ ፡ ሥጋሁ ፡ ለኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ባንድ ፡ ሥጋው ፡ ክሶ ፡ ኹለቱንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እቀረባቸው ፡ (አለ ፡) አስታረቃቸው ።

በመስቀሉ ።

(ገብረ ፡ ሰላመ ፡ በመስቀሉ ፡) ተሰቅሎ ፡ ባፈሰሰው ፡ ደሙ ፡ ኹለቱንም ፡ አንድ ፡ አደረጋቸው ።

ወለጽልዕ ፡ ቀተሎ ፡ ቦቱ ።

በመስቀል ፡ ድል ፡ ነሣው ፡ (ጽልዕ) አለው ፡ ዲያብሎስን ፡ በግብሩ ፡ ነው ።

ወመጽአ ፡ ወወሀበነ ፡ ሰላመ ፡ ለርኁቃን ፡ ወሰላመ ፡ ለቅሩባን ፡ (ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፱ ፡ ዘካ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡)

በመካከልም ፡ ኾኖ ፡ ከተስፋው ፡ ርቀን ፡ የነበርነውንና ፡ ወደተስፋው ፡ ቀርበን ፡ የነበርነውን ፡ አንድ ፡ አደረገን ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መርሐነ ፡ ወአቅረበነ ፡ ለክልኤነ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)

ኹለታችንንም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጆች ፡ አድርጎ ፡ ወደአባቱ ፡ አቅርበናልና ፤ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ አስታርቆናልና ።

እምይእዜሰ ፡ ኢኮንክሙ ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ።

ወነግዳን ፡ አንትሙ ፡ እምሥርዓተ ፡ ተስፋ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ከወንጌል ፡ መጻተ ኞች ፡ አይደላችሁም ።

አላ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገሪቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ለእግዚአከሐር ። (ም ፡ ፫ ፡ ፮ ፡ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።)

የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሰብእች ፡ የወንጌል ፡ ባለቤቶች ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ፡

እስመ ፡ ተሐንጽክሙ ፡ ዲበ ፡ መሠረተ ፡ ሐዋርያት ፡ ወነቢያት ። (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ ።)

ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ባስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ጸንታችኋልና ።

እንዘ ፡ ክርስቶስ ፡ ርእሰ ፡ ማዕዘንተ ፡ ሕንጻ ። (ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፲፮ ።)

ክርስቶስ ፡ ምእመናንን ፡ የሚያስተምሩ ፡ የመምህራን ፡ በኵር ፡ ሲኾን ፡ አንድም ፡ መልስ ።

እምይእዜሰ ፡ ኢኮንክሙ ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ መርሐነ ፡ ወአቅረበነ ፡ ለክልኤነ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ከልጅነት ፡ መጻተኞች ፡ ስደተኞች ፡ አይደላችሁም ።

አላ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገሪቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የልጅነት ፡ ባለቤት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሰቦች ፡ ናችሁ ፡ እንጂ ፡

እስመ ፡ ተሐንጽክሙ ፡ ዲበ ፡ መሠረተ ፡ ሐዋርያት ፡ ወነቢያት ።

ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ባመኑበት ፡ እምነት ፡ ጸንታችኋልና ።

እንዘ ፡ ክርስቶስ ፡ ርእሰ ፡ ማዕዘንተ ፡ ሕንጻ ።

እንዘ ፡ ክርስቶስ ፡ ርእሰ ፡ ሕንጻ ፡ ማዕዘንተ ፡ ብለህ ፡ አቅና ።

ሕንጻ ፡ ማዕዘንት ፡ ክርስቶስ ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ የምእመናን ፡ በኵር ፡ ሲኾን ።

ዘቦቱ ፡ የኀድር ፡ ኵሉ ፡ ሕንጻ ፡ ወይጸንዕ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ሕንጻ ፡ ጸንቶበት ፡ የሚኖር ፡ የእግዘአብሔር ፡ የመቅደሱ ፡ ጽርሕ ፡ የጸናበት ፡ (አለ) ፡ ምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ ምእመናን ፡ እስራኤል ፡ ጸንተውበት ፡ የሚኖሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወእንትሙሂ ፡ ቦቱ ፡ ተሐነጽክሙ ፡ ማኅደረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
እናንተም ፡ በመንፈስ ፡ ቅደስ ፡ ልጆች ፡ ኾናችሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመኾን ፡ ጸንታችሁበት ፡ ያለ ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ።

፩ ፡ ወእንበይነዝ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ ሙቁሕ ፡ ለክርስቶስ ፡ እንበይነ ፡ ዚአክሙ ፡ አሕዛብ ፡ (ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ።
እንበይነዝና ፡ እንበይነ ፡ ዚአክሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እናንተን ፡ በለማስተምር ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ የክርስቶስ ፡ እስሩ ፡ ነኝ ።

፪ ፡ ሶበ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ሀብተ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘወሀበኒ ፡ በእንቲአክሙ ።
ስለናንተ ፡ የሾመኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ በለጋስነት ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ በተቀበላችሁ ፡ ጊዜ ፡ የታሰርኩ ፡ እስሩ ፡ ነኝ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ክሡተ ፡ ሊተ ፡ ምክሮ ፡ ወአርአየኒ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)
ሥጋዌውን ፡ ገልጦልኛልና ።
በከመ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ኅዳጠ ።
ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ከምሉ ፡ በከፍሉ ፡ እንደጻፍሁላችሁ ።

፬ ፡ በዘትክሉ ፡ አእምሮ ፡ ሶበ ፡ ታነብቡ ።
በተመለከታችሁ ፡ ጊዜ ፡ ማወቅ ፡ በሚቻላችሁ ፡ ገንዘብ ።
ወተአምሩ ፡ ሐሊናየ ፡ በምክሩ ፡ ለክርስቶስ ።
ልቡናዬም ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋዌውን ፡ በማወቅ ፡ ጸንቶ ፡ እንዳለ ፡ በምታውቁ ፡ ገንዘብ ።

፭ ፡ ዘኢየአምር ፡ ካልእ ፡ ትውልድ ።
ሌላ ፡ ትውልድ ፡ የማያውቀው ።
ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።
ካልእ ፡ ትውልድ ፡ ያለውን ፡ ደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ብሎ ፡ ደገመ ።
ከመ ፡ ይእዜ ፡ ተከሥተ ፡ ለቅዱሳኒ ፡ ሐዋርያት ፡ ወነቢያቲሁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። (ም ፡ ፮ ፡ ፱ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ ዛሬ ፡ እንደተገለጠ ፡ ክሡተ ፡ ሊተ ፡ እንደተገለጠ ፡ ዘኢየአምር ፡ ካልእ ፡ ትውልድ ።

፮ ፡ ከመ ፡ ይረስዮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ መዋርስቲሁ ፡
አሕዛብን ፡ ተወራሾቹ ፡ ተካፋዮቹ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ።
ወሥጋሁ ።
አካሉ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ።
ወይኅበሩ ፡ ተስፋ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌል ። (ም ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።)
በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚገኘው ፡ ተስፋ ፡ አንድ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።

፯ ፡ ዘሎቱ ፡ ተሠየምኩ ፡ አነ ፡ ላእከ ፡ ወገብሮ ።
እኔ ፡ ለሩቁ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ለቅርቡ ፡ አስተማሪ ፡ እንድም ፡ ለብዙው ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ለጥቂቱ ፡ አስተማሪ ፡ የተሾምሁለት ።
በከመ ፡ ሀብተ ፡ ጸጋሁ ፡ ዘወሀበኒ ፡ ሊተ ፡ በረድኤተ ፡ ኃይሉ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፯ ።)
በቸሐሊነቱ ፡ አጋዥነት ፡ እንደሚያገዘኝ ፡ እንደአጋዥነቱ ፡ ስጦታ ፡ መጠን ፡
ሊተ ፡ ዘእነ ፡ እቴሐት ፡ እምኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ወሀበኒ ፡ ዘንተ ፡ ጸጋሁ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)
ከሐዋርያት ፡ ኹሉ ፡ ለማንስ ፡ ለኔ ፡ ይህን ፡ ሐዋርያነት ፡ ሾመኝ ።

፰ ፡ ከመ ፡ እምሀርሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ (ገላ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።)
ለአሕዛብ ፡ የክርስቶስን ፡ ብዕል ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ አስተምራቸው ፡ ዘንድ ።
ዘአልቦ ፡ አሠር ።
ባሕርዩ ፡ የማይመረመር ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ ፡ ወአብርሆ ፡ ለኵሉ ።

ለኹሉ ፡ በሥጋ ፡ የተገለጠ ፡ ብሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ቀጠለ ። እንድም ፡ ዘአልቦ ፡ ፀሐር ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ። ብሎ ፡ ለብዕል ፡ ቀጠለ ፡ ወአብርሃ ፡ ሲል ፡ ከመእምሀርሙ ፡ ወከመ ፡ አብርሃ ፡ ለኵሉ) ፡ ለኹሉ ፡ እንልጣት ፡ ዘንድ ፡ ወሀበኒ ። ምንት ፡ ውእቱ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ምክር ።

የዚህ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ (አመ) ፡ ደግ ፡ እንደሆነ ፡ ለአሕዛብ ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

ዘኅቡዕ ፡ እምዓለም ፡ በኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ፈጠረ ። (ሮሜ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ፡ ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡)

ኹሉን ፡ በፈጠረ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታውቆ ፡ ያለ ፡ ኅቡዕ ፡ ከሰው ፡ ነው ።

፲ ፡ ከመ ፡ ይእዜ ፡ ይትዐወቅ ፡ ለቀደምት ፡ ወለመኳንንት ፡ እለ ፡ በሰማያት ፡ በእንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።)

ምእመናንን ፡ ስለማስተማር ፡ በሰማያዊ ፡ ማዕርግ ፡ ላሉ ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ እስኪገለጥ ፡ ኅቡዕ ፡ የነበረ ። እንድም ፡ ምእመናንን ፡ ስለማስተማር ፡ በሰማያዊ ፡ ማዕርግ ፡ ላሉ ፡ ለቀሳውስትና ፡ ለዲያቆናት ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ከመ ፡ እምሀርሙ ።

ጥበቢሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫ ።)

ጥበቢሁ ፡ ብሎ ፡ ለሥጋዌ ፡ ቀጠለ ።

እንተ ፡ ብዙኅ ፡ ኅበሪያ ።

ኅብረ ፡ ትውልዱ ፡ ኅብረ ፡ አማኒዋ ፡ ኅብረ ፡ ባሕርይዋ ፡ ብዙ ፡ የሚኾን ፡ ኅብረ ፡ ትውልድ ፡ ኅብረ ፡ አማኒ ፤ ከሕዝብ ፡ ከአሕዛብ ፤ ከሕቃል ፤ ከሀገሬት ፡ ነው ።

ኅብረ ፡ ባሕርይ ፡ ሐማሚ ፤ ኢሐማሚ ፤ መዋቲ ፤ ኢመዋቲ ፤ ነው ፡ እንድም ፡ ጥበቢሁ ፡ ብሎ ፡ ለወንጌል ፡ ቀጠለ ፡ እንተ ፡ ብዙኅ ፡ ኅበሪሃ) ፡ ኅብረ ፡ ተቀባይዋ ፡ ኅብረ ፡ ሥርዓቷ ፡ ብዙ ፡ የሚኾን ፡ ኅብረ ፡ ተቀባይ ፡ ከሕዝብ ፡ ከአሕዛብ ፤ ከሐቃል ፡ ከሀገሬት ። ኅብረ ፡ ሥርዓት ፤ የወጣኒ ፤ የማእከላዊ ፡ የፍጹም ፤ አለና ፡ እንድም ፡ ጥበቢሁ ፡ ብሎ ፡ ለምእመን ፡ ቀጠለ ፡ (እንተ ፡ ብዙኅ ፡ ኅበሪሃ ፡ ኅብረ ፡ ነገዱ ፡ ኅብረ ፡ ተዋልጦተ ፡ ገድሏ ፤ ኅብረ ፡ መዐርጓ ፡ ብዙ ፡ የሚኾን ፡ ኅብረ ፡ ነገድ ፤ ከሕዝብ ፡ ከአሕዛብ ፤ ከሐቃል ፤ ከሀገሬት ፤ ኅብረ ፡ ተዋልጦተ ፡ ገድል ፡ የእሳት ፤ የሰለት ፤ አለና ፤ ኅብረ ፡ መዓርግ ፡ የሰባት ፤ የዘጠኝ ፡ የዐሥራኹለት ፡ አለና ።

፲፩ ፡ ዘሠርዓ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ያከናወናት ።

ወፈጸማ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)

ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ የወሰናት ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የፈጸማት ።

፲፪ ፡ ዘቦቱ ፡ ረከብነ ፡ ጸጋ ፡ ወሞገስ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፮ ።)

ልጅነትን ፡ ባለሟልነትን ፡ ያገኘንበት ።

ወመርሀነ ፡ ውስተ ፡ ተስፋ ፡ ዘሃይማኖት ።

እምነ ፡ ወደሚገኘው ፡ ክብር ፡ መርቶ ፡ ያደረሰበት ።

፲፫ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እስተበቍዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይትቈጥዓ ፡ ለሕማምየ ፡ እንተ ፡ ረከበተኒ ፡ በእንቲአከሙ ፡ ለክብርክሙ ፡ (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።)

ስለዚህም ፡ እናንተ ፡ ልትከብሩባት ፡ ስለናንተ ፡ ያገኘችኝን ፡ መከራዩን ፡ አልሻሽም ፡ እንዳይላት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እማልደዋለሁ ።

፲፬ ፡ ወእሰግድ ፡ ለአብ ፡ በብረክየ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፫ ።)

ስለዚህም ፡ ለአብ ፡ በብርክ ፡ ልቡናዬ ፡ እሰግዳለሁ ፡ ብርክ ፡ ሥጋው ፡ ታስሯልና ፡ እሰግድ ፡ በብረክ ፡ ልብየ ፡ አለ ።

፲፭ ፡ ዘኪያሁ ፡ ይጼውዑ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ዘበሰማያት ፡ ወዘበምድር ።

በሰማይ ፡ በምድር ፡ መንድረው ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ የሚለምኑት ።

፲፮ ፡ ከመ ፡ የሀብክሙ ፡ በከመ ፡ ብዕለ ፡ ስብሐቲሁ ።

እንደጌትነቱ ፡ ብዛት ፡ ዕውቀቱን ፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወያጽንዕክሙ ፡ በኃይለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፰ ። ፪ ፡ ፰ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፲ ።)
በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ኃይል ፡ ያጸናችሁ ፡ ዘንድ ፡ እስተበቍዖ ፡ ላለው ።
የሀብክሙ ፡ በከመ ፡ ብዕለ ፡ ስብሐቲሁ ፤ (ያጽንዕክሙ ፡፤ በኃይለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ) ፡ ብሎ ፡ ኹለት ፡ እርእስት ፡ ተናግሯል ፡ ለኹለቱም ፡ ያመጣል ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ እንተ ፡ ውስጡ ፡ ለሰብእ ፡ የኀድር ፡ ክርስቶስ ፡ በሃይማኖት ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ በተፋቅሮ ፡ እንዘ ፡ ይከውን ፡ ሥርውክሙሂ ፡ ወመሠረትክሙሂ ። (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ።)
(ሥርውክሙ ፡ በሃይማኖት ፤ መሠረትክሙ ፡ በተፋቅሮ) ልቡናችሁ ፡ በሃይማኖት ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ በፍቅር ፡ የጸና ፡ ኾኖ ፡ ብትገኙ ፡ ክርስቶስ ፡ በሰው ፡ በውስጣዊ ፡ አእምሮው ፡ አድሮ ፡ ይኖራልና ፡ የሀብክሙ ።

፲፰ ፡ ከመ ፡ ትክሀሉ ፡ ረኪበ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ።
ከቅዱሳን ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ ማወቅን ፡ ሊታወቁ ፡ ዕውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ፡ እስተበቍዖ።
ምንትኑ ፡ ራኅቡ ።
ከሰሜን ፡ እስከ ፡ ደቡብ ።
ወኑኁ ።
ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ።
ወላዕሉ ።
ከምድር ፡ እስከ ፡ ጠፈር ።
ወዕመቁ ፡ (ኢዮ ፡ ፲፩ ፡ ፰ ፡ ፱ ።)
ከምድር ፡ እስከ ፡ በርባሮስ ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ሊታወቁ ፡ ዕውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ፡ እስተበቍዖ ።
አንድም ፡ ምንትኑ ፡ ራኅቡ ።
ከልጅ ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ቤት ።
ወኑኁ ።
ከአልጋ ፡ ጓሮ ፡ እስከ ፡ ደጃፍ ።
ወላዕሉ ።
ከወለሉ ፡ እስከ ፡ ውቅሩ ።
ወዕመቁ ።
ከውቅሩ ፡ እስከ ፡ ወለሉ ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ሊታወቁ ።
አንድም ፡ (ራኅቡ ፡) እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ መሰቀሉ ፡ (ኑኁ ፤) ቆሞ ፡ መሰቀሉ ። (ላዕሉ ፤) ከፍ ፡ ብሎ ፡ መሰቀሉ ። (ዕመቁ ፤) ወደመቃብር ፡ መውረዱ ፡ ምን ፡ እንደኾነ ።

፲፱ ፡ ለጠይቆ ፡ ብዝኀ ፡ አእምሮ ፡ ፍቅሩ ፡ ለክርስቶስ ።
የክርስቶስን ፡ የፍቅሩን ፡ ብዛት ፡ ማወቅ ፡ መጠን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደኾነ ፡ ለመረዳት ፡ ምን ፡ እንደ ኾነ ፡ (አለ ፡) ደግ ፡ እንደሆነ ፡ ሊታወቁ ፡ እውቀቱን ፡ ይገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ፡ እስተብቍዖ ።
ከመ ፡ ትሠለጡ ፡ በኵሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ፍጹምነት ፡ ባለው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹማን ፡ ልትኾኑ ፡ ያጸናችሁ ፡ ዘንድ ፡ እስተበቍዖ ።

፳ ፡ ዘይክል ፡ አጽንዖተክሙ ፡ ትግበሩ ፡ ኵሎ ። (ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፳፭ ።)
ኹሉን ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ እናንተን ፡ ማጽናት ፡ የሚቻለው ።
ወታፈድፍዱ ፡ ዘንስእል ፡ ወዘንሔሊ ።
የምንሻውን ፡ የምንለምነውን ፡ አብዝታችሁ ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ።
በከመ ፡ ይረድአነ ፡ ኃይሉ ።
ከሐሊነቱ ፡ እንደሚያግዘን ፡ መጠን ።

፳፩ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባመኑት ፡ በምእመን ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ።
በኵሉ ፡ ትውልድ ።
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለውን ፡ ኵሉ ፡ ትውልድ ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወለዓለመ ፡ ዓለም ። (ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፴፮ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፯ ።)
ለዘለዓለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ያለው ።
አሜን ። በእውነት ።

## ምዕራፍ ፬ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ አስተበቍዐክሙ ፡ አነ ፡ ሙቁሕ ፡ በክርስቶስ ።
በክርስቶስ ፡ ስም ፡ የታሰርኩ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ እማልዳችኋለሁ ።
ከመ ፡ ትሑሩ ፡ በዘይደልዋ ፡ ለጸዋዔክሙ ፡ ዘተጸዋዕክሙ ።
በሃይማኖት ፡ ንዑ ፡ ትልውኒ ፡ ተብላችሁ ፡ ለተጠራችሁት ፡ አጠራር ፡ በሚገባ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ በወልድ ፡ ውሉድ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብላችሁ ፡ ለተጠራችኋት ፡ አጠራር ፡ በሚገባ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ኋላ ፡ ንዑ ፡ ኅቤየ ፡ ተብላችሁ ፡ ለምትጠሯት ፡ አጠራር ፡ በሚገባ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።

፪ ፡ እንዘ ፡ ታቴሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ በኵሉ ፡ የውሃት ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)
በፍጹም ፡ ቅንነት ፡ ትሕትናን ፡ ይዛችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።
ወትትዔገሡ ።
እንዘ ፡ ትትዔገሡ ፡ መከራውን ፡ ታግሣችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።
ከመ ፡ ትትዓገሡ ፡ መከራውን ፡ ታግሣችሁ ፡ ትቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ አስተበቍዓክሙ ።
ወእሆ ፡ ትብሉ ፡ ለቢጽክሙ ።
እንዘ ፡ እሆ ፡ ትቤሉ ፤ እሺ ፡ በጄ ፡ እያላችሁ ፡ ትኑሩ ፡ ዘንድ ፡ ከመ ፡ እሆ ፡ ትብሉ ፡ እሺ ፡ በጄ ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ፡ አስተበቍዓክሙ ።
ወትጽሀቁ ፡ ለተፋቅሮ ።
(እንዘ ፡ ትጽሀቁ ፡) ለፍቅር ፡ ተግታችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፤ ለፍቅር ፡ ትተጉ ፡ ዘንድ ፡ አስተበቍዓክሙ ።
ወተኀበሩ ።
(እንዘ ፡ ተኃብሩ ፤) በፍቅር ፡ አንድ ፡ ኾናችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ከመ ፡ ትኅበሩ ፡ በፍቅር ፡ አንድ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አስተበቍዓክሙ ።

፫ ፡ ወትትዓቀቡ ፡ በአሐዱ ፡ መንፈስ ፡ ወበማእሰረ ፡ ሰላም ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።)
በፍቅር ፡ አንድነት ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ኾናችሁ ፡ ተጠብቃችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ትጠበቁ ፡ ዘንድ ።
፬ ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ አሐደ ፡ ሥጋ ፡ ወአሐደ ፡ መንፈሰ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፭ ።)
እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደነፍስ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ አንድ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ።
በከመ ፡ ተጸዋዕክሙ ፡ ለአሐዱ ፡ ተስፋክሙ ።
አንድ ፡ ተስፋችሁን ፡ ለማግኘት ፡ ተጠርታችሁ ፡ እንዳላችሁ ፡ መጠን ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ አሐደ ፡ ሥጋ ፡ ላለው ።

፭ ፡ አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ዘዳግ ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፬ ፡ ፮ ።)
እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አለ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡
እንድም ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አሐዱ ።
ወአሐቲ ፡ ሃይማኖት ።
ሃይማኖትም ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ በአብ ፡ ስም ፡ በወልድ ፡ ስም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ቢያምኑ ።
ወአሐቲ ፡ ጥምቀት ።
ጥምቀትም ፡ አንዲት ፡ ናት ። በአብ ፡ ስም ፡ በወልድ ፡ ስም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ቢጠመቁ ። በ፵ ፡ ቀን ፡ በ፹ ፡ ቀን ፤ በ፵ ፡ ዘመን ፡ በ፹ ፡ ዘመን ፡ ቢጠመቁ ፤ በዓቢይ ፡ ባሕር ፤ በንኡስ ፡ ባሕር ፡ ቢጠመቁ ። በሊቀ ፡ ጳጳስ ፤ በጳጳስ ፤ በኤጲስ ቆጶስ ፤ በቄስ ፡ እጅ ፡ ቢጠመቁ ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፡ ወእሑዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለኵሉ ፡ (ሚልክ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፮ ።)
ለኹሉ ፡ አባት ፡ የሚኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (አለ ፡) በተሰየ ፡ አካሉ ፡ አንድም ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ እሑዱ ።

ዘላዕለ ፡ ኵሉ ።
ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ።

ወእምኔሁ ፡ ኵሉ ።
ኹሉ ፡ ከሱ ፡ የተገኘ ።

ወውእቱ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ።
በኹሉ ፡ በምላት ፡ የሚኖር ።

፯ ፡ ወለለአሐዱ ፡ እምኔነ ፡ ተውህበ ፡ ጸጋሁ ፡ በመሥፈርተ ፡ ሀብቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ሮሜ፡ ፲፪ ፡ ፫ ፡ ፩፡ቆሮ ፲፪፡ ፲፩ ።)
ክርስቶስ ፡ ሀብቱን ፡ እየሰፈረ ፡ በሚያድልበት ፡ መስፈሪያ ፡ ከኛ ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ ጸጋው ፡ ተሰጠ።

፰ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ ዐረገ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ጼዊወከ ፡ ጼዋ ፡ (መዝ፡ ፷፯ ፡ ፲፱ ፡ መሳ ፡ ፭ ፡ ፲፪፡ ቆላ ፡ ፪፡ ፲፭ ።)
ይህን ፡ አይሻውም ።

ወወሀብከ ፡ ጸጋከ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።
ወሀብከ ፡ ጸጋከ ፡ እንዳለ ፡ ተውህበ ፡ ጸጋሁ ።

አንድም ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ ዐረገ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ጼዊወከ ፡ ጼዋ ።
ጼዋ ፡ ነፍሳትን ፡ ማርከህ ፡ በተነሣህ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ አረግህ ።

ወወሀብከ ፡ ጸጋከ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፫ ።)
ባረግህ ፡ በዐሥር ፡ ቀን ፡ በተነሣህ ፡ በእምሳ ፡ ቀን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለሐዋርያት ፡ ሰጠህ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ ተውህበ ፡ ጸጋሁ ።

፱ ፡ ወምንትኑ ፡ እንከ ፡ ዕርገቱ ፡ ሶበ ፡ ኢወረደ ፡ መትሕተ ፡ ምድር ፡ (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።)
ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ካልወረደ ፡ ዐረገ ፡ መባሉ ፡ ምንድነው ።

፲ ፡ ዘወረደሂ ፡ ውእቱ ፡ ወዘዐርገሂ ፡ ውእቱ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፬ ።)
የወረደውም ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ያረገውም ፡ እሱ ፡ ነው ።

አንድም ፡ ወምንትኑ ፡ እንከ ፡ ዕርገቱ ፡ ሶበ ፡ ኢወረደ ፡ መትሕተ ፡ ምድር ።
ሰው ፡ ካልኾነ ፡ ከበረ ፡ መባሉ ፡ ምንድነው ።

ዘወረደሂ ፡ ውእቱ ፡ ወዘዐርገሂ ፡ ውእቱ ።
ሰው ፡ የኾነውም ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ከበረ ፡ የተባለውም ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ ወደመቃብር ፡ ካልወረደ ፡ ተነሣ ፡ መባሉ ፡ ምንድነው ። ወደመቃብር ፡ የወረደውም ፡ እሱ ፡ ነው ፡ የተነሣውም ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወዘህሉ ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ኵሎ ።
ኹሉን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ እስኪፈጽም ፡ በልዕልና ፡ ያለ ።

፲፩ ፡ ወውእቱ ፡ ወሀበ ፡ ጸጋ ፡ ወከፈለ ።
ጸጋውን ፡ ከፍሎ ፡ ከፍሎ ፡ ያደለ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወረሰየ ፡ እምሰብእ ፡ ዚአሁ ፡ ሐዋርያተ ።
ከ፻፳ውም ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ፲፪ቱን ፡ መርጠ ፡ የሾመ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወእምኔሆሙ ፡ ነቢያተ ።
ሰብአ ፡ አርድእትን ፡ መርጠ ፡ የሾመ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወመምህራነ ፤ ኤጲስቆጶሳትን ።
ወእምኔሆሙ ፡ ኖሎተ ፤ ቀሳውስትን ።
ወእምኔሆሙ ፡ ሊቃውንተ ፤ መተርጕማንን ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳፩ ፡ ፰ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ።)

፲፪ ፡ ወበዘይጸንዑ ፡ ቅዱሳን ፡ ለግብረ ፡ መልእክቱ ።
ቅዱሳን ፡ መምህራን ፡ ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ በሚጸኑ ፡ ገንዘብ ።

ወለሕንጸ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
ምእመናንን ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ ማኅበር ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ለማድረግ ፡ አንድም ፡ ለግብረ ፡ መልእክቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይላል ፡ ቅዱሳን ፡ ምእመናን ፡ ጌትነቱን ፡ ለማገልገል ፡ በሚጸኑ ፡ ገንዘብ ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፤ ማኅበር ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ለመኾን ።

፲፫ ፡ እስከ ፡ ንከውን ፡ ኵልነ ፡ አሐደ ፡ በሃይማኖት ።
ኹላችንም ፡ በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ እስክንኾን ፡ ድረስ ።
ወበአእምሮቱ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ።
ወልደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማወቅ ፡ አንድ ፡ እስክንኾን ፡ ድረስ ።
ወንኩን ፡ ከመ ፡ ዘአሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ብጹሐ ፡ አምጣን ፡ በዕቅመ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ለክርስቶስ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።)

በክርስቶስ ፡ ፈጻሚነት ፡ በሚገኝ ፡ ዕውቀት ፡ ልክ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ እንዳደረሰው ፡ እንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ፍጹሙ ፡ ሰው ፡ እንኹን ። እንድም ፡ ክርስቶስ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ እድርሶ ፡ በመጣት ፡ ልጅነት ፡ እንዳንዱ ፡ እንደፍጹሙ ፡ ሰው ፡ እንኹን ። አንድም ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ እንኹን ፡

፲፬ ፡ ከመ ፡ ኢንኩን ፡ እንከ ፡ ደቂቀ ፡ ዘይትነትን ፡ ወይትሐወስ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ነፋስ ፤ በምግበ ፡ ነፋስ ፡ እንዳለ ፡ ብላቴና ፡ እንዳንኾን ።
ቃለ ፡ ትምይንተ ፡ ትምህርተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ አለ ፡ ይትመነገኑ ፡ በጕሕሉቶሙ ፡ ከመ ፡ ያስሕቱ ።
በተንኰላቸው ፡ ሰውን ፡ ያስቱ ፡ ዘንድ ፡ የሚተነኩሉ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ወደሚያስተምሯት ፡ ስውሥራሽ ፡ ትምህርት ፡ ወደእሪት ፡ ለመመለስ ፡ በምግበ ፡ ነፋስ ፡ እንዳለ ፡ ብላቴና ፡ እንዳንኾን ።
፲፭ ፡ አላ ፡ ንጽደቅ ፡ እንከ ፡ በተፋቅሮ ።
ፀፍቅር ፡ እንጽና ፡ እንጂ ።
ወንብጻኅ ፡ በኵሉ ፡ ዘብነ ፡ ፀክርስቶስ ።
ከክርስቶስ ፡ ባገኘነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ፍጹማን ፡ እንኹን ፡ እንጂ ።
አንድም ፡ (ጽደቂ) በፍቅር ፡ ጽኑ ፡ እንጂ ፡ (ብዝኁ) ፡ ከክርስቶስ ፡ ባገኘነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ፍጹማን ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ።
ዘውእቱ ፡ ርእስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳ ፡ ፳፫ ። ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።)
በኵሮ ፡ የሚኾን ፡ ብሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ይቀጥላል ።

፲፮ ፡ ዘቦቱ ፡ የኃድር ፡ ኵሉ ፡ ሥጋ ።
ሥጋ ፡ ጸንቶበት ፡ የሚኖር ፡ ብሎ ፡ ለሰው ፡ ይቀጥላል ።
ወይትዋደድ ፡ በኵሉ ፡ ሥርው ።
በጅማት ፡ አንድ ፡ የሚኾንበት ።

በበመሥፈርተ ፡ ሀብቱ ፡ ዘይትወሀብ ፡ ለለአሐዱ ፡ መሌሊት ፡ እምን ፡ መለያልይ ።
ከሕዋሳት ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ ሕዋስ ፡ በሚሰጠው ፡ ስጦታ ፡ ልክ ።
በዘይልሕቅ ፡ ሥጋ ፡ ወይትፈጸም ።
ሥጋ ፡ በሚያድግ ፡ በሚፈጸም ፡ ገንዘብ ። የወርድ ፡ ፤ የቁመት ፤ የረጅም ፡ የአጥር ፤ የወፍራም ፤ የቀጭን ፡ አለና ፡ ይደጋግማል ።
ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ሕንጻሁ ፡ በተፋቅሮ ፡ (ቈላ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ።)
ሕንጻው ፡ ባንድነት ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ።
ዘቦቱ ፡ የኃድር ፡ ኵሉ ፡ ሥጋ ።
አንድም ፡ ምእመናን ፡ ጸንተውበት ፡ የሚኖሩ ፡ ብሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ይቀጥላል ።
ወይትዋደድ ፡ በኵሉ ፡ ሥርው ።
በፍቅር ፡ አንድ ፡ የሚኾኑበት ።
በበመሥፈርተ ፡ ሀብቱ ፡ ዘይትወሀብ ፡ ለለ፩ ፡ ፩ ፡ መሌሊት ፡ እምን ፡ መለያልይ ።
ከምእመናን ፡ ላንዱም ፡ ላንዱም ፡ በሚሰጠው ፡ ስጦታ ፡ ልክ ፡ በፍቅር ፡ አንድ ፡ የሚኾኑበት ።
በዘይልሕቅ ፡ ሥጋ ፡ ወይትፌጸም ።
የወጣኒ ፡ የማእከላዊ ፡ የፍጹም ፡ አለና ፡ ይደጋግማል ።
ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ሕንጻሁ ፡ በተፋቅሮ ።
አንድነቱ ፡ በፍቅር ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክ ፍ ል ፡ ፭ ።

፲፯ ፡ ዘንተ ፡ እብል ፡ ወእሰምዕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በእንቲአከሙ ።
በናንት ፡ እንዲህ ፡ እያልሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እዳኛለሁ ። ወደእግዚአብሔር ፡ እያዳኘሁ ፡ እን
ዲህ ፡ እላለሁ ።
ከመ ፡ ኢትሑሩ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በሕሊና ፡ ልቦሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።)
ልቡናቸው ፡ በወደደው ፡ ሥራ ፡ እንደሚኖሩ ፡ እንደአሕዛብ ፡ እትኑሩ ፡ ብዬ ።

፲፰ ፡ ወጽሉም ፡ ሕሊናሆሙ ።
ልቡናቸው ፡ እፍን ፡ ጭፍን ፡ ያለ ።
ወነኪራን ፡ እምሕይወተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕበዶሙ ። (ም ፡ ፱ ፡ ፲፯ ።)
በስንፍናቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚያወርሳቸው ፡ ክብር ፡ የተለዩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡
የተለዩ ።
ወበጽላሌ ፡ ልቦሙ ።
በልቡናቸው ፡ ድንቍርና ፡ የተለዩ ።

፲፱ ፡ እለ ፡ ቅቡጻን ፡ ተስፋሆሙ ።
ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ የሌላቸው ።
ወመጠዉ ፡ ርእሶሙ ፡ ለሕርትምና ።
ራሳቸውን ፡ ለጥፋት ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡ ።
ወለርኩስ ፡ ለኃጢአት ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡ ።
ወለምርዓት ፡ ድርዓት ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡ ።

፳ ፡ ወአንትሙሰ ፡ አኮ ፡ ከማሁ ፡ ዘተምሀርክምዎ ።
እናንተ ፡ ግን ፡ ክርስቶስን ፡ የተማራችሁት ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ።

፳፩ ፡ ወእመሰ ፡ አማነ ፡ ትሰምዕዎ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።)
(እመሰ) ፡ ) እንዲሁም ፡ ካልሆነ ፡ (አማነ ፡ ትሰምዕዎ) ፡ በውነት ፡ ትሰሙታላችሁ ፡ ወትትሚሀሩ ፡
ማንሻ ።
ወትትሚሀሩ ፡ በኀቤሁ ፡ ጽድቀ ።
በውነት ፡ የምትሰሙት ፡ ከኾነ ፡ ጽድቅን ፡ ከሱ ፡ ትማራላችሁ ።
እስመ ፡ ጽድቅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ።
ጽድቅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ። (እዕትቱ) ፡ ማንሻ ።

፳፪ ፡ አዕትቱ ፡ እምላዕሌክሙ ፡ ግዕዘክሙ ፡ ዘትካት ።
ጽድቅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ፡ ጽድቅን ፡ ከሱ ፡ የምትማሩ ፡ ከኾነ ፡ ብሉይ ፡ ግብርን ፡ ከናንተ ፡
አርቁ ።
ብሉይ ፡ ግብርን ፡ ከናንተ ፡ አርቁ ።
እብል ፡ በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ብእሲ ፡ ዘይማስን ፡ በፍትወተ ፡ ስሒት ። (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፯፯ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ፡ ቆላስ ፡ ፫ ፡ ፱ )
አረትን ፡ ኃጢአትን ፡ በመውደድ ፡ ስለሚለወጥ ፡ ሰውነት ፡ እንዲህ ፡ እላለሁ ።

፳፫ ፡ ሐድሱ ፡ መንፈሰ ፡ ልብክሙ ። (ገላት ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።)
ልቡናችሁን ፡ በዕውቀት ፡ እድሱ ፡ እላለሁ ።

፳፬ ፡ ወልበስዎ ፡ ለሐዲስ ፡ ብእሲ ፡ ዘሐደሶ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ፡ ወበንጽሕ ። (ዘፍጥ ፡
፩ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ።)
እግዚአብሔር ፡ በጸድቅ ፡ በንጽሕ ፡ በርትዕ ፡ ያደሰው ፡ ሐዲስ ፡ ኢዲስ ፡ ቆጳስን ፡ ምሰሉት ። አንድም ፡
እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ በርትዕ ፡ በንጽሕ ፡ ያጸናው ፡ ሐዲስ ፡ ብእሲ ፡ ክርስቶስ ን ፡ ምሰሉት ።

፳፭ ፡ ወበእንተዝ ፡ ኅድግዋ ፡ ለሐሰት ፡ ወተናገሩ ፡ ጽድቀ ፡ ኵልክሙ ፡ ምስለ ፡ ቢጽክሙ ።
ስለዚህ ፡ ሐሰትን ፡ ትታችሁ ፡ በሃይማኖት ፡ ከመሰሏችሁ ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ ጋራ ፡ እውነት ፡ ነገ
ርን ፡ ተጫዋወቱ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ አሐዱ ፡ እባል ፡ ንሕነ ።
እንድ ፡ አካል ፡ ነንና ።

፳፮ ፡ ተምዑ ፡
ጊዜ ፡ ቢያነሣሣችሁ ፡ ተቆጡ ።

ወኢተፀብሱ ።   (መዝ ፡ ፬ ፡ ፳ ፡ ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።)
ደቅር ፡ ሳትሉ ፡ ግን ፡ እትደሩ ። ወዘእንበለ ፡ ይዕርብ ፡ ፀሐይ ፡ እቍርሩ ፡ መዓትክሙ ፡ ብሎ ፡ አሁን ፡ እንዲያመጣው ። አንድም ፡ በሚገባ ፡ ተቆጡ ፡ በመዓት ፡ ዘበርትዕ ፡ እንዲል ፡ (አፈ ፡ ወር) ፡ የሚገባ ፡ ቁጣ ፡ አለና ። ሕፃናት ፡ አንማርም ፡ ቢሉ ፡ የተማሩትን ፡ ቢገድፉ ፡ መናፍቃን ፡ በጉባኤ ፡ እንዳይ ሠለጥኑ ፡ ምእመናን ፡ ከሃይማኖት ፡ እንዳይወጡ ፡ ከምግባር ፡ እንዳይናወጡ ።

ወኢተአብሱ ።
በማይገባ ፡ ግን ፡ አትቆጡ ።

ወዘእንበለ ፡ ይዕርብ ፡ ፀሐይ ፡ አቍርሩ ፡ መዓትክሙ ።
ፀሐይ ፡ ሳይገባ ፡ ቍጣችሁን ፡ አቀዝቅዙ ፡ (አለ) ፡ ይቅር ፡ ሳትሉ ፡ አትደሩ ። አንድም ፡ ፀሐይ ፡ ዕድሜያችሁ ፡ ሳለ ፡ ከኃጢአት ፡ ተመለሱ ።

፳፯ ፡ ወኢተሀብዎ ፡ ፍኖተ ፡ ለሰይጣን ።
ለሰይጣን ፡ ምክንያት ፡ አትስጡት ።

፳፰ ፡ ዘይሰርቅኒ ፡ ኢይሰርቅ ፡ እንከ ።
የሰው ፡ ከብት ፡ የሚያነሣሣም ፡ እያነሣሣ ።

ለይትገበር ፡ ወይጻሙ ፡ እንከ ፡ በእደዊሁ ፡ ለሠናይ ፡ በዘይረድእ ፡ ለነዳይ ፡   (፩ ፡ ተሰሎ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።)
ነዳይ ፡ ሰውነቱን ፡ በሚረዳው ፡ ገንዘብ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዞ ፡ ይመገብ ፡ እንጂ ፡ (ለሠናይ ፡) ተግባረ፡ እድ ፡ መያዙ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ሊኾንለት ። እንድም ፡ ደኅውን ፡ በሚረዳው ፡ ገንዘብ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይያዝ ፡ እንጂ ፡ (ለሠናይ ፡) ተግባረ ፡ እድ ፡ መያዙ ፡ መርዳቱ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ሊኾንለት ።

፳፱ ፡ ወኵሉ ፡ ነገር ፡ ኅሡም ፡ ኢይፃእ ፡ እምአፉክሙ ።   (ም ፡ ፭ ፡ ፬ ።)
ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ባንደበታችሁ ፡ አይነገር ።

ዘእንበለ ፡ ሠናይ ፡ በዘይትሐነጽ ፡ ትካዝክሙ ።   (ቈላ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ና ፡ ፬ ፡ ፯ ።)
ግዳጃችሁ ፡ በሚፈጸም ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈጸምበት ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ እንጂ ።

ከመ ፡ ይርከቡ ፡ ሞገሰ ፡ እለ ፡ ይሰምዑክሙ ።
የሚሰሟችሁ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ድኅነትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ።

፴ ፡ ወኢታምዕዕዎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘቦቱ ፡ ዐተበክሙ ፡ እመ ፡ ድኅንክሙ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፲ ።)
ባመናችሁ ፡ ጊዜ ፡ እናንተን ፡ ከኢአማንያን ፡ የለዩበትን ፡ ራሳቸውን ፡ ያስመሰሉበትን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርታችሁ ፡ እንዲለያችሁ ፡ አታድርጉ ።

፴፩ ፡ ወኵሎ ፡ መሪረ ።
የሚያሳዝን ፡ ነገርን ፡ ሁሉ ።

ወመዓተ ፤   ብስጭትን ።
ወቍጥዓ ፤   ቍጣን ፤
ወመርገመ ፤   መራገምን ፤
ወመንሡተ ፤   ጠብ ፡ ክርክርን ፤
ወፅርፈተ ፤   ስድብን ፤
እዕትቱ ፡ እምላዕሌክሙ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ እኩይ ።   (ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፰ ።)
ከክፋው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ ከናንት ፡ አርቁ ።

፴፪ ፡ ወኩኑ ፡ መሐርያነ ፡ ቢጽክሙ ።
ለወንድሞቻችሁ ፡ የምታዝኑ ፡ የምትራሩ ፡ ኹኑ ።

ወተጻገዉ ፡ በበይናቲክሙ ።
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ይቅር ፡ ተባባሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

በከመ ፡ ጸገወክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ። (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፱ና ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።)
እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ። (አለ) ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ እንደሰጣችሁ ። ማለቱ ፡ ነው ። እንድም ፡ ወተጸገወ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተረዳዱ ፡ ከብት ፡ ለሌለው ፡ ከብት ፡ ጉልበት ፡ ለሌለው ፡ ጉልበት ፡ (በከመ ፡ ጸገወክሙ ፡) እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ እንደረዳችሁ ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፭ ።

፩ ፡ ተመሰሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ውሉድ ፡ ፍቁራን ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፭ ፡)
ውሉድ ፡ ፍቁራን ፡ እንደመኾናችሁ ፤ እንድም ፡ እንደውሉድ ፡ ፍቁራን ፡ እንደሐዋርያት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምሰሉት ።

፪ ፡ ወሑሩ ፡ በተፋቅሮ ። (ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ፡ ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲ ።)
በፍቅር ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ።
ከመ ፡ ዘአፍቀረከሙ ፡ ክርስቶስ ።
ክርስቶስ ፡ እንደወደዳችሁ ።
ወመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአከሙ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለመዓዛ ፡ ሠናይ ።
መውደዱም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ልጅነትን ፡ ለመስጠት ፡ ጸጋን ፡ ለማምጣት ፡ እንድም ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ራሱን ፡ ስለኛንት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳቀረበ ።

፫ ፡ ወዝሙትሰ ፤ — ዝሙት ፡ ግን ።
ወዅሉ ፡ ርኩስ ፡ — ኃጢአት
ወትዕግልት ፡ — ቅሚያ ።
ኢይሰማዕ ፡ በላዕሌክሙ ።
አይሰማባችሁ ።
በከመ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ (ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።)
አለማሰማቱ ፡ ለቅዱሳን ፡ እንዲገባ ፡ (ኢይደልዎሙ ።) መስማቱ ፡ ለቅዱሳን ፡ እንዳይገባቸው ።

፬ ፡ ወኢነገረ ፡ ኃፍረት ።
የሚያሳፍር ፡ ነገር ።
ወነገረ ፡ ዕበድ ፡ — የስንፍና ፡ ነገር ።
ወነገረ ፡ ስላቅ ፡ ዘኢይደሉ ። ም ፡ ፬ ፡ ፳፱ ።
የዋዛ ፡ የፈዛዛ ፡ ነገር ፡ አይሰማባችሁ ። እንድም ፡ ነገረ ፡ ኃፍረት ፤ ሥርዓተ ፡ ረበናት ። ነገረ ፡ ዕበድ ፤ ሥርዓተ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ነገረ ፡ ስላቅ ፡ ሥርዓተ ፡ ሰዱቃውያን ።
ዘኢይደሉ ፡ ብሎ ፡ ለኹሉም ፤ ቀጠለ ። እንድም ፡ (ወዘኢይደሉ ፡) የማይገባም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ።
ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ እእኵቶ ፡ ሀየንተዝ ፡ እኩይ ።
ስለዚህ ፡ ስለከፋው ፡ ግብር ፡ ፈንታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማመስገን ፡ ይሰማባችሁ ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ወዘንተ ፡ አእምሩ ፡ — ይህንም ፡ ዕወቁ ።
ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘማዊ ፡ — ሴሰኛ ።
ወርኩስ ፡ — ኃጢአተኛ ።
ወመስተዐግል — የሰው ፡ ከብት ፡ የሚቀማ ።
ወዘያጣዑ ፡ — ጣዖት ፡ የሚያመልክ ።
አልቦ ፡ መክፈልት ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)
የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚያድላት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ጽዋዕ ፡ ተርታ ፡ እንደሌለው ፡ ዕወቁ ። እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ልጁ ፡ በክርስቶስ ፡ በሚያድላት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ጽዋዕ ፡ ተራ ፡ እንደሌለው ፡ ዕወቁ ።

፮ ፡ አልቦ ፡ ዘያስሕተክሙ ፡ በነገረ ፡ ከንቱ ።
በነገር ፡ ከንቱ ፡ በነገረ ፡ ከንቱ ፡ ይላል ፡ በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ የሚያስታችሁ ፡ አይኑር ።
እስመ ፡ በእንቲእሁ ፡ ይመጽእ ፡ መዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ውሉደ ፡ ዐላውያን ።
ላዕለ ፡ ውሉድ ፡ ዐላውያን ። ላዕለ ፡ ውሉደ ፡ ዓላውያን ፡ ይላል ፡ በሱ ፡ ምክንያት ፡ በዐላውያን ፡ ልጆች

www.ethiopianorthodox.org

ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘ ፡ መቅሠፍት ፡ ይመጣልና ፡ እልቦ ፡ ዘያስሕተክሙ ፡ (አንድም ፡ ዘበእንቲአሁ) ፡ በሱ ፡ ምክንያት ፡ በዐላውያን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘ ፡ መቅሠፍት ፡ የሚመጣበት ።

፯ ፡ ኢትትመሰልዎሙኬ ፡
እንደነዚህ ፡ ያሉትንም ፡ እብነት ፡ እታድርጓቸው ።

፰ ፡ እስመ ፡ ትካት ፡ ጽልመት ፡ እንትሙ ።
ቀድሞ ፡ ዐላዋቆች ፡ ነበራችሁና ።
ወይእዜሰ ፡ ብርሃን ፡ ኮንክሙ ፡ በእግዚእን ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱ ።)
ዛሬ ፡ ግን ፡ በጌታችን ፡ ዐዋቆች ፡ ኾናችኋልና ፡ ኢትትመሰልዎሙኬ ፡

፱ ፡ ከመ ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ ሑሩ ፡ እንከሰ ።
እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ እንደመኾናችሁ ፤ እንድም ፡ እንደውሉደ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ በዕውቀት ኑሩ ።
እስመ ፡ ፍሬሁ ፡ ለብርሃን ፡ ኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ወጽድቅ ፡ ወርትዕ ። (ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፰ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ።)
የዕውቀት ፡ ፍሬው ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ነውና ። ጽድቅ ፡ ነውና ። ርትዕ ፡ ነውና ፡ ከመ ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ ሑሩ ።

፲ ፡ ወአመክሩ ፡ ዘያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ቍ ፡ ፲፯ ፡ ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።)
እግዘአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ሥራ ፡ መርምራችሁ ፡ ያዙ ፡ መመርመር ፡ ከመጻሕፍት ከመምህራን ፡ ከልቡና ።

፲፩ ፡ ወኢትኅበሩ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ እልቦሙ ፡ ፍሬ ፡ ምግባሮሙ ።
በጎ ፡ ምግባር ፡ ከሌላቸው ፡ እንድም ፤ ሥራቸውን ፡ ገልጠው ፡ ከማይሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አትሁኑ
ዘጽልመት ፡ ኵለንታሆሙ ፤
ሥራቸው ፡ እፍን ፡ ጭፍን ፡ ያለ ።
እላ ፡ ገሥጽዎሙ ፡ ምከሯቸው ፡ አስተምሯቸው ፡ እንጂ ።

፲፪ ፡ እስመ ፡ ዘበጽሚት ፡ ይገብሩ ፡ ኃፍረተ ፡ ለነጊር ። (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።)
እንድም ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ (ኃፍረቅ ፡ ለነጊር) የረበናትን፡ ሥርዓት ፡ ለማስተማር፡ ነውና፡
እንድም ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ኃፍረት ፡ ለነጊር ፡ ሊናገሩት ፡ ያሳፍራልና ።

፲፫ ፡ ወዘሰ ፡ ክሡት ፡ ኵሉ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ይትዐወቅ ። (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።)
ተገልጦ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ የዕውቀት ፡ ሥራ ፡ እንደኾነ ፡ ይታወቃል ።
እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘገሃድ ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ።
ተገልጦ ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ የዕውቀት ፡ ሥራ ፡ ነውና ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ ንቃህ ፡ ዘትነውም ።
አይኛውም ፡ ወተንሥእ ፡ እሙታን ፡ እይኛውም ።
ወያበርህ ፡ ለከ ፡ ክርስቶስ ፡ (ኢሳ ፡ ፷ ፡ ፩ ፡ ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ።)
ያበርህ ፡ ለከ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳለ ፤ ወዘሰ ፡ ክሡት ፡ ኵሉ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ።
እንድም ፡ ወዘሰ ፡ ክሡት ፡ ኵሉ ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ይትዐወቅ ።
ሥራውን ፡ ገልጦ ፡ የሚሠራ ፡ ዐዋቂ ፡ እንደኾነ ፡ ይታወቃል ።
እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘገሃድ ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ።
ሥራውን ፡ ገልጦ ፡ የሚሠራ ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ።
እስመ ፡ ይቤ ፡ ንቃህ ፡ ዘትነውም ፤ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ንቃ ።
ወተንሥእ ፡ እሙታን ፤ ከሙታን ፡ ሕሊና ፡ ተለይተህ ፡ ተነሣ ።
ወያበርህ ፡ ለከ ፡ ክርስቶስ ።
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕውቀቱን ፡ ይገልጥልሃል ፡ ብሏልና ፡ ወዘሰ ፡ ክሡት ፡ ኵሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ላለው ፤
ወይእዜስ ፡ ብርሃን ፡ ኮንከሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ከመ ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ ሑሩ ፡ ላለውም ፡ ብትስጥ ፡ ይመቻል ።

፲፫ ፡ ዑቁ ፡ እንከ ፡ ዘከመ ፡ ተሐውሩ ፡ ከመ ፡ ጠቢባን ፡ በንጽሕ ።
እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ጠቢባን ፡ እንደመኾናችሁ ፡ በንጽሕና ፡ ጸንታችሁ ፡ እንድትኖሩ ፡ ዕወቁ ።
ወአኮ ፡ ከመ ፡ አብዳን ፡ (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ። ቆላ ፡ ፬ ፡ ፭ ።)
ሰነፎች ፡ እንደመኾናችሁ ፡ ያይደለ ። አንድም ፡ ከመ ፡ ጠቢባን ፡ እንደጠቢባን ፡ እንደሐዋርያት ፡ በንጽሕና ፡ ጸንታችሁ ፡ እንድትኖሩ ፡ ዕወቁ ።
ወአኮ ፡ ከመ ፡ አብዳን ።
እንደሰነፎች ፡ እንደጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ያይደለ ።

፲፬ ፡ እንዘ ፡ ታነሐስይዎ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ።
ይህን ፡ ዓለም ፡ እየናቃችሁት ፡ እያቃለላችሁት ።
እስመ ፡ እኩይ ፡ መዋዕሊሁ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ።)
ዘመኑ ፡ ጥቂት ፡ ነውና ።

፲፭ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢትኩኑ ፡ አብዳነ ።
ስለዚህ ፡ ዐላዋቆች ፡ አትኹኑ ።
አላ ፡ ሐልዩ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ቍ ፡ ፲ ።)
እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ሥራ ፡ መርምራችሁ ፡ ያዙ ፡ አንድ ፡ መመርመር ፡ ከመጻሕፍት ፡ ከመምህራን ፡ ከልቡና ።

፲፮ ፡ ወኢትስክሩ ፡ ወይነ ፡ (ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፴፬ ።)
ወይን ፡ አብዝታችሁ ፡ አትጠጡ ፡
እስመ ፡ ምርዓት ፡ ውእቱ ።
ድርዓት ፡ ነውና ።
አላ ፡ ምልኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱስ ።
በወይኑ ፡ ቦታ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተመሉ ፡ እንጂ ።

፲፱ ፡ ወእንብቡ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ድገሙ ።
ወስብሐተ ፡ ስብሐተ ፡ ሙሴን ።
ወማኅሌተ ፡ ቅድሳት ።
ከአራቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሰሎሞን ፡ የተለየ ፡ አምስቱን ፡ መሐልይ ፡ አንድም ፡ (ወማኅሌተ) ፡ አምስቱን ፡ መሐልይ ፡ (ወቅድሳተ ፡) ከእንቀጸ ፡ ብፁዓን ፡ የተለየ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ድገሙ ።
ሰብሑ ፡ ወዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በልብክሙ ፤ (መዝ ፡ ፴፫ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ቆላስ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።)
በልቡናችሁም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

፳ ፡ እዕኩቱ ፡ ዘልፈ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አብ ።
በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ስለተደረገላችሁ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ኹልጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ አመስግኑት ።

## ክ ፍ ል ፡ ፭ ።

፳፩ ፡ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለቢጽክሙ ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፭ ።)
ሠሪዐ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፤ በትሕትና ፡ ይጀምራል ፤ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹናችሁ ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ ታዘዙ ፡ ተገዙ ።

፳፪ ፡ ወአንስትኒ ፡ ይትአዘዛ ፡ ለአምታቲሆን ።
ሴቶችም ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይታዘዙ ፡ ይገዙ ።
ከመ ፡ ዘለእግዚእነ ። (ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። ቆላስ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፩ ) ፤
ለጌታችን ፡ እንደሚገዛ ። አንድም ፡ ለጌታችን ፡ እንደሚገዙ ፡ ይገዙ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ርእሳ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።
ክርስቶስ ፡ ለምእመን ፡ ገዥዋ ፡ ጌታዋ ፡ እንደኾነ ።

፳፫ ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ርእሳ ፡ ለብእሲት ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ።)
ለሴትም ፡ ገዥዋ ፡ ጌታዋ ፡ ባሏ ፡ ነውና ።
ወመድኀኒ ፡ ሥጋ ።
ክርስቶስ ፡ ለምእመን ፡ መኖሪያዋ ፡ መገኛዋ ፡ እንደኾነ ፡ ለሴትም ፡ መኖሪያዋ ፡ መገኛዋ ፡ ባሏ ፡ ነውና ፡ ትታዘዝ ።

፳፬ ፡ ወከመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትትኤዘዞ ፡ ለክርስቶስ ።
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምእመን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንድትታዘዝ ።
ከማሁ ፡ አንስትኒ ፡ ይትአዘዛ ፡ ለአምታቲሆን ፡ በኵሉ ።
ሴቶችም ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይታዘዙ ፡ ይገዙ ፤ (በኵሉ) ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ በውስጥ ፡ በአፍኣ ።

፳፭ ፡ እደውኒ ፡ ያፍቅሩ ፡ አንስቲያሆሙ ፡
ትእዛዝ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አይደለምና ፡ ወንዶችም ፡ ምሽቶቻቸውን ፡ ይውደዱ ።
ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ አፍቀራ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።
ክርስቶስ ፡ ምእመንን ፡ እንደወደዳት ።
ወመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአሃ ፡ (ቆላስ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።)
መውደዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ስለስዋ ፡ ራሱን ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ እንደሰጠ ።

፳፮ ፡ ከመ ፡ ይቀድሳ ፡ ወያንጽሓ ፡ በጥምቀተ ፡ ማይ ፡ በማየ ፡ ገቦ ።
ወበቃሉ ፡ (ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭ ።)
ዘአምነ ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ ንጽሕት ፡ ክብርት ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ። (አንድም ፡ በጥምቀተ ፡ ማይ ፡ በቃሉ) ፡ ዘአምነ ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፡ ባለው ፡ ጥምቀት ፡ ንጽሕት ፡ ክብርት ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ።

፳፯ ፡ ወይረስያ ፡ ሎቱ ፡ ክብርተ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ።
ምእመንን ፡ ለሱ ፡ የከበረች ፡ ማደሪያ ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ።
መጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአሃ ።
ከመ ፡ ኢይርከብ ፡ በላዕሌሃ ፡ ርስሐተ ፡ ወጥልቀተ ።
አፍአዊ ፡ ውሳጣዊ ፡ ኃጢአትን ፡ እንዳያገኝባት ።
ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ንጽሕተ ፡ ወቅድስተ ፡ (መዝ ፡ ፵፭ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፪ ።)
ንጽሕት ፡ ክብርት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ ኢይርከብ ።

፳፰ ፡ ከማሁ ፡ ዕደውኒ ፡ ያፍቅሩ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ከመ ፡ ነፍሶሙ ።
እንደዚህም ፡ ወንዶች ፡ እንደራሳቸው ፡ አድርገው ፡ ምሽቶቻቸውን ፡ ይውደዱ ።
ዘአፍቀረ ፡ ብእሲቶ ፡ ርእሶ ፡ አፍቀረ ።
ምሽቱን ፡ የወደደ ፡ ራሱን ፡ ወደደ ።

፳፱ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ጸሊዓ ፡ ሥጋሁ ፡ ግሙራ ።
ከቶ ፡ ራሱን ፡ መጥላት ፡ የሚቻለው ፡ የለም ።
ሴስዩ ። ወጥታችሁ ፡ ወርዳችሁ ፡ መግቡ ።
ወተማኅፀኑ ። ሕፃን ፡ ጀንደረባ ፡ ሰጥታችሁ ፡ አስጠብቁ ።
በከመ ፡ ክርስቶስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ።
ሴሰያ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ክርስቶስ ፡ ለምእመን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ እንደመገበ ። አንድም ፡ (ሴስዩ ፡ ለብእሲትኒ ፡ ዘበርቱዕ ፡ ይግበር ፡ ላቲ ፡ ምታ ፡ ያለውን ፡ ለሌላ ፡ አታድርጉባቸው ።
ወተማኅፀኑ ፡ በከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ።
ክርስቶስ ፡ ምእመንን ፡ ለመምህራን ፡ እንዳስጠበቀ ፡ ሕፃን ፡ ጀንደረባ ፡ ሰጥታችሁ ፡ (ተማኅፀኑ ፡) አስጠብቁ ።

፴ ፡ እስመ ፡ አባለ ፡ ሥጋሁ ፡ ንሕነ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፳፫ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፭ ።)
አንድ ፡ አካል ፡ ነንና ፡ ብላችሁ ፡ ተማኅፀኑ ። አንድም ፡ እስመ ፡ አባለ ፡ ሥጋሁ ፡ ይእቲ ፡ ይላል ፡ አካሉ ፡ ናትና ።

www.ethiopianorthodox.org

ወበእንተዝ ፡ የኀድግ ፡ ብእሲ ፡ እባሁ ፡ ወእሞ ፡ ወይትልዋ ፡ ለብእሲቱ ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ እናቱን ፡ አባቱን ፡ ትቶ ፡ ምሽቱን ፡ ይከተላታል ፡ ሀገሯ ፡ ቆላ ፡ ቢኾን ፡ ቆላ ፡ ይወርዳል ፡ ደጋ ፡ ቢኾን ፡ ደጋ ፡ ይወጣል ። አንድም ፡ (ይተልዋ ፡) በግብር ፡ ነው ፡ ወይተለዋ ፡ እባግዐ ፡ ቀርሜሎስ ፡ እንዲል ፡ ይትሳጸቃ ፡ ሲል ፡ (ሐተታ) ፡ እኅ ፡ ፈቃድ ፡ ቢነግበት ፡ ከእናቴ ፡ ከእኅቴ ፡ ሳድርገው ፡ አይልምና ። እኂም ፡ ፈቃድ ፡ ቢነግባት ፡ ከአባቴ ፡ ከወንድሜ ፡ ሳድርገው ፡ አትልምና ።

ወይከውኑ ፡ ክልኤሆሙ ፡ እሐደ ፡ ሥጋ ።   (ዘፍጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፭ ።)

እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ፡ አካል ፡ ይኾናሉ ፡ ( አለ ፡ ) በግብር ። አንድም ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ በማስገኘት ፡ ወንድ ፡ ቢወልዱ ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ ሴት ፡ ቢወልዱ ፡ ያንች ፡ ናት ፡ አይባባሉም። አንድም ፡ አባታቸውን ፡ ቢመስሉ ፡ ያንተ ፡ ናቸው ፡ እናታቸውን ፡ ቢመስሉ ፡ ያንች ፡ ናቸው ፡ አይባባሉምና ፡ አንድም ፡ በወዲሁ ፡ ሀሥራት ፡ በኵራት ፡ አውጥተው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ ቢኖሩ ፡ በወዲያውም ፡ አንድ ፡ ዓለም ፡ ክርስቶስን ፡ ወርሰው ። አንድ ፡ ፀሐይ ፡ ክርስቶስን ፡ ሙቀው ፡ ይኖራሉና ።

፴፪ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ ዝነገር ።

ይህ ፡ የመርዓትና ፡ የመርዓዊ ፡ ቀዋሕዶ ፡ ደግ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ።

ወአንስ ፡ እብሎ ፡ ሳዕለ ፡ ክርስቶስ ።

ለክርስቶስና ፡ ለምእመናን ፡ ምሳሌ ፡ አድርጌ ፡ እናገራለሁ ፤ መርዓዊን ፡ ለክርስቶስ ። መርዓትን ፡ ለምእመን ። አንድም ፡ ሳዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባለው ፡ አብቅቶ ፡ ለመለኮትና ፡ ለትስብእት ፡ ምሳሌ ፡ አድርጌ ፡ እናገረዋለሁ ፡ መርዓዊን ፡ ለመለኮት ፡ መርዓትን ፡ ለትስብእት ።

ወላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ወላአለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲል ፡ መርዓዊን ፡ ለክርስቶስ ፡ መርዓትን ፡ ለምእመን ።

፴፫ ፡ ወባሕቱ ፡ አንትሙኒ ፡ ኵልክሙ ፡ ከማሁ ፡ አንስቲያክሙ ፡ አፍቅሩ ፡ ከመ ፡ ነፍስክሙ ።

አንኪያስ ፡ እናንተ ፡ ሁላችሁም ፡ እንደራሳችሁ ፡ አድርጋችሁ ፡ ምሽቶቻችሁን ፡ ውደዱ ።

ወብእሲትኒ ፡ ትፍርሆ ፡ ለምታ ።

ሴትም ፡ ባሏን ፡ ትፍራው ፡ ታክብሬው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፮ ።

፩ ፡ ውሉድኒ ፡ ተእዘዙ ፡ ለእዝማዲክሙ ፡ በእግዚእነ ፡   (ቆላ ፡ ፫ ፡ ፳ ።)

ልጆችም ፡ እክብር ፡ እባክ ፡ ወአመክ ፡ ባለው ፡ በጌታችን ፡ ትእዛዝ ፡ ለእናት ፡ ለአባታችሁ ፡ ታዘዙ ፡ ተገዙ ።

እስመ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ።

ለእናት ፡ ለእባት ፡ መታዘዝ ፡ ደግ ፡ ነውና ።

፪ ፡ ወቀዳሚ ፡ ትእዛዝ ፡ ውእተ ፡ ሥርዓት ።   (ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ።)

በአሪት ፡ መጀመሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ (አለ ።)

አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ።

እናት ፤ እባትን ፡ መርዳት ፡ ነውና ።

፫ ፡ ከመ ፡ ሠናየ ፡ ይኩንከ ።

መርዳቱ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ይኾንልሀ ፡ ዘንድ ።

ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።

ሠናየ ፡ ይኩንከ ፡ ያለውን ፡ ይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ። ዕድሜ ፡ ይበዛልሀ ፡ ዘንድ ።

ወቀዳሚ ፡ ትእዛዝ ፡ በውስተ ፡ ኦሪት ፡ አክብር ፡ እባከ ፡ ወእመከ ።

አንድም ፡ በአሪቱ ፡ መጀመሪያው ፡ (ደገኛው ) ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ነውና ።

ከመ ፡ ሠናየ ፡ ይኩንከ ።

ሌላ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ይኾንልሀ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።
ዕድሜህም ፡ ይበዛልህ ፡ ዘንድ ።

፬ ፡ አበውኒ ፡ ኢታስተቈጥዑ ፡ ውሉደክሙ ።
አበውም ፡ ብጽብጾኞች ፡ ኾናችሁ ፡ ልጆቻችሁን ፡ እንዲመረሩ ፡ እንዲበሳጩ ፡ አታድርጓቸው ። አንድም ፡ ልጆቻችሁን ፡ ሳትሠሩ ፡ ሳትቀጡ ፡ አሳድጋችሁ ፡ ሠርቀው ፡ ቀምተው ፡ እንዲሰቀሉ ፡ እንዲቆረጡ ፡ አታድርጉ ።
አላ ፡ ሐፅኑ ፡ ወገሥጹ ፡ በትምህርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ዘዳግ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ መዝ ፡ ፸፰ ፡ ፬ ፡ ምሳ ፡ ፲፱፡ ፲፰)
(ቆላ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።)
(አንድም ፡ መልስ ፡) አበውኒ ፡ ኢታስተቈጥዑ ፡ ውሉደክሙ ።
ሠርታችሁ ፡ ቀጥታችሁ ፡ አሳድጉ ፡ እንጂ ። ልጆቻችሁን ፡ ሳትመክሩ ፡ ሳታስተምሩ ፡ አሳድጋችሁ ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ እንዲባሉ ፡ አታድርጉ ።
አላ ፡ ሐፅኑ ፡ ወገሥጹ ፡ በትምህርተ ፡ እግዚአብሔር ።
መቅድመ ፡ መሀርዎሙ ፡ መጽሐፈ ፡ ሰሎሞን ፡ ወሲራክ ፡ ወዳዊት፡ ባለው፡ መክራችሁ፡ አስተምራችሁ ፡ አሳድጓቸው ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ነባርኒ ፡ ተአዘዙ ፡ ለአጋእዝቲክሙ ፡ እለ ፡ ይኲንኑክሙ ፡ ሥጋክሙ ።
ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ በሥጋችሁ ፡ ለሚገዟችሁ ፡ ለጌቶቻችሁ ፡ ታዘዙ ፡ ተገዙ ።
በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ።
በፍርሃት ፡ በረዓድ ፡ ኾናችሁ ፡ (አለ ፡) በእንገዛ ፡ ተገዙ ፡ ያለ፡ እግዚአብሔር፡ ይፈርድብናል፡ ብላችሁ ።
አንድም ፡ ጌቶቻችሁን ፡ ፈርታችሁ ።
ወበልብ ፡ ስቱሕ ።
ልባችሁን ፡ አስፍታችሁ ።
ከመ ፡ ዘለክርስቶስ ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።)
ለክርስቶስ ፡ እንደሚገዛ ፡ እንደምትገዙ ።

፮ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዘያደሉ ፡ ለዓይነ ፡ ሰብእ ።
ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እንደሚገዛ ፡ ያይደለ ።
አላ ፡ ከመ ፡ አግብርተ ፡ ክርስቶስ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ፈቃዶ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ እንደሚፈጽሙ ፡ እንደ ፡ አግብርተ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደሐዋርያት ። አንድም (እለ ፡ ትገብሩ ፡ ) የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ የምትፈጽሙ ፡ አግብርተ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደመኾናችሁ ፡ ተገዙ ፡ እንጂ ።

፯ ፡ ወበኵሉ ፡ ነፍስክሙ ፡ ተቀነዩ ፡ ሎሙ ፡ በአፍቅሮ ።
በፍጹም ፡ ሰውነታችሁ ፡ በፍቅር ፡ ኾናችሁ ፡ ተገዙላቸው ።
ከመ ፡ ዘለእግዚአብሔር ።
ለእግዚአብሔር ፡ እንደሚገዛ ። አንድም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደምትገዙ ፡ ተገዙላቸው ።
ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዘለሰብእ ።
ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እንደሚገዙ ፡ ያይደለ ። አንድም ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እንደምትገዙ ፡ ያይደለ ።

፰ ፡ እንዘ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሠናየ ፡ ይትዐሠይ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር፡ (፪ ፡ ቆሮ፡ ፭ ፡ ፲ ።)
በጎ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋውን ፡ እንዲያገኝ ፡ ዐውቃችሁ ።
ኢመኒ ፡ ነባሪ ።
ቤተ ፡ ሰብእም ፡ ቢኾን ።
ወእመኒ ፡ እግአዚ ።
ጌታም ፡ ቢኾን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ እንዲያገኝ ፡ ዐውቃችሁ ።

፱ ፡ ወአጋእዝትኒ ፡ ዕሩየ ፡ ግበሩ ፡ ሎሙ ፡ (ቆላ ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
ጌቶችም ፡ ቤተሰቦቻችሁን ፡ አስተካክሏቸው ፡ (አለ) ፡ ክራላችሁ ። (ሐተታ) ፡ ሥጋ ፡ ብንበላ ፡ ሥጋ ፡ ይብሉ ፡ ጠጅ ፡ ብንጠጣ ፡ ጠጅ ፡ ይጠጡ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ እንዲርበን ፡ ይርባቸዋል ፡ እንዲጠማን፡

www.ethiopianorthodox.org

ይጠግቸዋል ፡ እንዲያርዘን ፡ ያርዛቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንድም ፡ ከልጆቻችሁ ፡ ጋራ ፡ አስተካክሏቸው ። እንድም ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ አስተካክሏቸው ።

እንዘ ፡ ታቀርሩ ፡ መዓተክሙ ።
ከቍጣችሁ ፡ ታግሣችሁ ።
ወተኀድጉ ፡ ሎሙ ፡ አበሳሆሙ ።
ቢበድሏችሁ ፡ ይቅር ፡ ብላችሁ ።
ቶእምሩ ፡ ከመ ፡ ብከሙ ፡ እግዚእ ፡ በሰማያት ፡ ዘኢያደሉ ፡ ለገጽ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፴፬ ፡)
በበላያችሁ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያደላ ፡ ጌታ ፡ እንዳለ ፡ ታውቃላችሁና ።

## ክ ፍ ል ፮ ።

፲ ፡ እንከሰ ፡ ጽንዑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ከኾነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በማመን ፡ ጽኑ ።
ወበጽንዐ ፡ ኀይሉ ፡ (፩፡ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።)
በክሀሊነቱ ፡ አጋዥነት ፡ ጽንታችሁ ፡ ድል ፡ ንሡ ።

፲፩ ፡ ወልበሱ ፡ ወልታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘትክሉ ፡ ተቃውሞቶ ፡ ለመናምግተ ፡ ሰይጣን ። (፪፡ቆሮ፡ ፲፡ ፬ ።)
ሰይጣን ፡ ተተንኩሎ ፡ የሚያመጣባችሁን ፡ ጦር፡ ድል፡ መንሣት ፡ በሚቻላችሁ ፡ ገንዘብ ፡ አሳባሽ ፡ ጋሻ ፡ ያዙ ፡ (አለ) ፡ ሃይማኖትን ፡ ያዙ ።

፲፪ ፡ እስመ ፡ ቀትልክሙ ፡ ኢኮነ ፡ ምስለ ፡ ዘሥጋ ፡ ወደም ፡ (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፴፡ ኤፌ ፡ ፪፡ ፪ ፡)
ሰልፋችሁ ፡ ከሥጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ አይደለምና ።
ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ መኳንንተ ፡ ጽልመት ፡ ወአጋንንት ፡ እኩያን ፡ አለ ፡ መትሕተ ፡ ሰማይ ።
በአራቱ ፬ መዓዝን ፡ ካሉ ፡ ዓለመ ፡ ጽልመትን ፡ ከሚገዙ ፡ ከአጋንንት ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወበእንተዝ ፡ ንሥኡ ፡ ወልታ ፡ እግዚአብሔር ።
ስለዚህም ፡ ወልታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዙ ፡ ( አለ ፡ ) ሃይማኖትን ፡ ያዙ ።
ከመ ፡ ትክህሉ ፡ ተቃውሞታ ፡ ለዕለት ፡ እኪት ።
ዕለት ፡ እኪትን ፡ መቃወም ፡ ይቻላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ( ሐተታ ) ፡ መቃወም ፡ እንዳይገኙ ፡ መኾን ፡ ቢገኙም ፡ እንዳይጎዱ ፡ መኾን ፡ ነው ። ዕለት ፡ እኪት ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠሩባት ፡ ቀን ፡ ናት ፡ እንድም፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ናት ።
ወኩኑ ፡ ድልዋነ ፡ በኵሉ ፡ ከመ ፡ ትጽንዑ ።
ድል ፡ ትነሡ ፡ ዘንድ ፡ በሥራው ኹሉ ፡ የተዘጋጃችሁ ፡ ኹኑ ። ፣

፲፬ ፡ ቁሙ ፡ እንከ ፡ ቀኒቶክሙ ፡ ሐቌክሙ ፡ በጽድቅ ፡ (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ፡ ፩፡ ጴጥ፡፩ ፡ ፲፫ ።)
ወገባችሁን ፡ በጽድቅ ፡ ዝናር ፡ ታጥቃችሁ ፡ ኑሩ ፡ ( አለ ፡ ) ንጽሕናን ፡ ይዛችሁ ፡ ኑሩ ።
ወልበሱ ፡ ልብሰ ፡ ሐጺን ፡ ዘጽድቅ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፯ ።)
የጽድቅ ፡ ጥሩር ፡ ልበሱ ፡ ( አለ ፡ ) ትዕግሥትን ፡ ያዙ ።

፲፭ ፡ ተስኢነክሙ ፡ ኀይለ ፡ ወንጌል ፡ ዘበሰላም ።
ኃይል ፡ የሚኾናችሁ ፡ ጫማን ፡ ተጫምታችሁ ፡ አለ ፡ ምግባረ ፡ ወንጌልን ፡ ይዛችሁ ።
፲፮ ፡ ወምስለዝ ፡ ኵሉ ፡ ንሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ዘሃይማኖት ፡
ይህም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የበዳ ፡ ጸብት ፡ ያዙ ፡ አለ ፡ እምና ፡ የሚጠመቁትን ፡ ጥምቀትን ያዙ ።

በዘትክሉ እጥፍአተ ፡ ኵሉ ፡ አሕጻሁ ፡ ለእኩይ ፡ ርሱን ፡ (፩፡ ጴጥ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ ፩፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፬ ።)
እንደእሳት ፡ የሚነድ ፡ የሰይጣንን ፡ ፍላጻ ፡ ማጥፋት ፡ በሚቻላችሁ ፡ ገንዘብ ፡ ጥምቀትን ፡ ያዙ ፡( ሐተታ በአርበኛ ፡ አምሳል ፡ ተናገረ ፡ የወዲያኛው ፡ ቀስቱን ፡ እያተባ ፡ እያጋለ ፡ መርዝ ፡ እየቀባ ፡ ይመጣል ፡ የወዲህኛውም ፡ ጥበቡን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገልጦለት ፡ ጆባውን ፡ ከውኃ ፡ ነክሮ ፡ ለጋሻው ፡ አልብሶ ፡ ይይዛል ፡ ስለቱን ፡ ጋሻው ፡ ይገታለታል ፡ መርዙን ፡ ጆባው ፡ ይጠርግለታል ፤ ግለቱን ፡ ውኃው፡ ያቀዘቅዝለታል ። እንደዚህም ፡ ኹሉ ፡ ከጥምቀት ፡ ባገኙት ፡ ኃይል ፡ ድል ፡ ይነሡታልና ።
፲፯ ፡ ወንሥኡ ፡ ጌራ ፡ መድኃኒት ፡ ሳዕለ ፡ ርእስክሙ ፡ (፩፡ ተሰሎ ፡ ፭ ፡ ፰ ።)
በራሳችሁም ፡ ቦርቦርቴ ፡ ድፉ ፡ አለ ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤን ፡ ያዙ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወሰይፈ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንሥኡ ፡ በእደዊክሙ ፡
　　በእጃችሁም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሰይፍ ፡ ያዙ ፡ ( እሱ ፡ ) በቃላችሁ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት፡ ድገሙ።
ዘውእቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
　　ይኸውም ፡ ወንጌል ፡ ነው ፡ ( ሐተታ ፡ ) በሥጋዊ ፡ አርበኛ ፡ አምሳል ፡ ተናገረ ፤ እስራኤል ፡ ከግብጽ፡ ሲወጡ ፡ ይህን ፡ አድርገው ፡ ወጥተዋልና ፡ ጫማቸውን ፡ አድርገው ፡ ኩፌታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝናራቸውን ታጥቀው ፤ በሎታቸውን ፡ ይዘው ፡ ( ወጥተዋል ፡ )
　　አንድም ፡ በመንፈሳውያን ፡ አርበኞች ፡ አምሳል ፡ ተናገረ ፡ እንደቦርቦርቴ ፡ ቆብዕ ፤ እንደጦር ፡ እን ካሴ ፤ እንደጥሩር ፡ መጋረፊያ ፤ እንደዝናር ፡ ያስፋ ፡ መቃድ ፤ እንደጫማ ፡ ነጠላ ፡ ጫማ ፡ እንደጋሻ ፡ ተረ ንተር ፡ አድርገው ፡ ወጥተው ፡ ወርደው ፡ ረቂቃን ፡ ጠላቶቻቸው ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ ይነሣሉና ።

፲፰ ፡ በኵሉ ፡ ጸሎት ፡ ወስእለት ፡
　　በምትጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ በምትለምኑት፡ ልመና ፡ ኹሉ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ድገሙ ።
እንዘ ፡ ትጼልዩ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ በመንፈስ ፡ ትጉሁ ፡ ወተፀመዱ ፡ ለጸሎት ፡ ኵሉ ፡ ጊዜ ፡
　　በጊዜያቱ ፡ ኹሉ ፡ ( እሱ ፡ ) በ፫ቱ ፤ በ፲፪ቱ ፤ በ፳፬ ፤ ጊዜያት ፡ ስትጸልዩ ፡ በልቡና ፡ ተግታችሁ ፡ ለጸ ሎት ፡ ኹልጊዜ ፡ ጽሙዳን ፡ ኹናችሁ ፡ ኑሩ ።
በእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ።
　　ስለቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ጸልዩ ።

፲፱ ፡ ወበእንቲአየ ፡　　ስለኔም ፡ ጸልዩ ።
ከመ ፡ የሀበኒ ፡ ቃለ ፡ (ቈላስ ፡ ፬ ፡ ፫ ። ፪ ተሰሎ ፡ ፫ ፡ ፩ ። )
　　ኃይለ ፡ ቃል ፡ ይገልጥልኝ ፡ ዘንድ ።
ወይከሥት ፡ አፉየ ።　　　　አፌን ፡ መልቼ ፡ እንድናገር ፡ ያደርገኝ ፡ ዘንድ ።
ከመ ፡ እንግር ፡ ገሀደ ፡ ሕርመተ ፡ ትምህርት ፡ ( ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፬ ፡ ፴፱ ።
　　በወንጌል ፡ የተጻፈ ፡ ሥጋዌን ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ( ትምህርተ ፡ ሕርመት ፡ ) ሥጋዌን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

፳ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ እተነብል ፡ ሙቁሕየ ፡　　　　ታስሬ ፡ የምጸልይበት ።
ከመ ፡ እንግር ፡ ገሀደ ፡ በእንቲአሁ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ እንግር ፡ ( ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፳ ። )
　　ማስተማር ፡ እንደሚገባኝ ፡ ገልጬ ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

፳፩ ፡ ወዘትፈቅዱሰ ፡ ታአምሩ ፡ አንትሙኒ ፡ ዜናየ ፡ ዘከመ ፡ እገብር ፡ ኵሉ ።
　　ኹሉን ፡ እንድሠራ ፡ የኔን ፡ ነገር ፡ ልታውቁ ፡ የምትወዱ ፡ ከኾነ ።
ያጤይቀክሙ ፡ ጢኪቆስ ፡ እኁነ ፡ ዘናፈቅር ፡ ላእከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምእመን ።
　　　　(ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፬ ፡ ፪ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፳ ።)
　　የታመነ ፡ ወንድማችን ጢኪቆስ ፡ ያስረዳችኋል ፡ ( ያጤይቅሙ ) ያስረዳችሁ ፡
　　( ዘናፈቅር ) የምንወደው ፡ የእግዚአሔር ፡ አገልጋይ ፡ የሚኾን ።

፳፪ ፡ ዘፈነውኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ በእንተዝ ።
　　ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወደናንተ ፡ የሰደድሁት ።
ከመ ፡ ታአምሩ ፡ ዜናየ ፡　　　　የኔን ፡ ነገር ፡ ዐውቃችሁ ።
ወይትፈሣሕክሙ ፡ ልብክሙ ።　(ቈላስ ፡ ፬ ፡ ፰ ።)
　　ልባችሁንም ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወደናንት ፡ የሰደድሁት ፡ የኔን ፡ ነገር ዐውቃችሁ ፡ ልባችሁን ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፳፫ ፡ ሰላም ፡ ለአኃዊነ ፡ ወተፋቅሮ ፡ ምስለ ፡ ሃይማኖት ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክር ስቶስ ።
　　ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ከሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ዘንድ ፡ ለወንድሞቻችን ፡ ይደረግላችሁ ። (ሐተታ) ፡ ጳውሎስ ፡ ፍቅርን ፡ ከሃይማኖት ፡ አይለይም ፡ ውእ ቱሰ ያስተላጽቅ ፡ ሃይማኖተ ፡ ምስለ ፡ ፍቅር ፡ በመንፈስ ፡ መድምም ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ገጸ ፡ መካን ፡ እን ዲል ፡ (እፈ ፡ ወርቅ) ።

www.ethiopianorthodox.org

ወጸጋሁ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅርዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኢጥፍዓት ፨ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፤ ፲፬
እለ ፡ ያፈቅርዎ ፡ በኢጥፍዓት ፡ ጸጋሁ ፡ በኢጥፍዓት ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ እለ ፡ ያፈቅርዎ ፡ በኢጥፍዓት ፡ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ሳይለያዩ ፡ ለሚወዱት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ (ጸጋሁ ፡ በኢጥፍዓት) ፤ ጸጋው ፡ ባለመለያየት ፡ ይደረግላቸው ፨

አሜን ፡ በእውነት ፨

ተፈጸመት ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ኤፌሶን ፡ ወተጽሕፈት ፡ በሮሜ ፡ ወተፈነወት ፡ በእደ ፡ ጢኪቆስ ፨
በሮም ፡ የተጻፈች ፡ በጢኪቆስ ፡ እጅ ፡ ለኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ መልእክት ፡ (ደረሰች) ተፈጸመች ፨

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፨
እስከምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፨